ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ዓርብ
81ኛ ዓመት ቁጥር 336 ነሐሴ 6 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ




# “ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ
## አሁን ያለበት ደረጃ የኢትዮጵያን ብልፅግና ማንም ሲያስቆመው እንደማይችል ማሳያ ነው”

- ዶክተር ዐቢይ አሕመድ
የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አሁን ያለበት ደረጃ የኢትዮጵያ ብልፅግና እውን የሚሆንና ማንም ሊያስቆመው እንደማይችል ማሳያ መሆኑን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተናገሩ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በትናንትናው እለት በጉባ ተገኝተው የታላቁ ኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን የሁለተኛ ዩኒት ኃይል ማመንጨት ባስጀመሩበትና አጠቃላይ የህዳሴ ግድብ የስራ ውጤትን በማስመልከት ለኢትዮጵያውያን ባስተላለፉት የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክታቸው፣ በታሪክ ውስጥ ማለፍ ዕድል እንደሆነ ነገር ግን ታሪክ ሠርቶ ማለፍ ዕድልም ድልም መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ይህም የዛሬይቱ የኢትዮጵያውያን ለአንድ ሺህ ዓመታት ሲታለም በቆየው፣ በርካቶችም ሲመኙት የነበረው የአባይን ውሃ የመጠቀም መሻት በዓይኑ ያየ፣ በእጁም የዳሰሰ እንዲሁም በእግሩ መርገጥ የቻለ ባለዕድል ትውልድ ስለሚያደርገው መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በርካታ ኢትዮጵያውያን ገንዘባቸውንና እውቀታቸውን ከዚህም አልፎ ሕይወታቸውን የገበሩለት ፕሮጀክት እንደሆነ ገልጸው፤ ስራው በዚህ ፍጥነት እንዳይከናወን ከፍተኛ ተግዳሮቶች የገጠሙትና የፀጥታ አካላትም በዚህ ልክ ብዙ ዋጋ የከፈሉበት መሆኑን አውስተዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ስፍራ በድል መቆማችንን አቅልለን ሳንመለከት ለላቀው ድል ደግሞ ዜጎች ከዚህ ይበልጥ እንዲነሳሱ አሳስበዋል፡፡

አባቶቻችን ይህንን ግድብ ለመገንባት አስበዋል፣ አልመዋል፣ እንዲሁም ብዙ ቁጭት አስተናግደዋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ነገር ግን እኛ የታለመውንና

“ታላቁ የኢትዮጵያ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# “በቀጣይ ሁለት ተኩል ዓመታት ግድቡን ሙሉ ለሙሉ ለማጠናቀቅ ታስቦ እየተሰራ ነው”

- ኢንጂነር ክፍሌ ሆሮ
የታላቁ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ዋና ስራ አስኪያጅ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የታላቁ ኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታን በቀጣይ ሁለት ተኩል ዓመታት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ለማጠናቀቅ ታስቦ እየተሰራ መሆኑን የታላቁ ህዳሴ ግድብ ዋና ስራ አስኪያጅ ኢንጂነር ክፍሌ ሆሮ ገለጹ፡፡ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም 83 ነጥብ ሦስት በመቶ መድረሱንም ጠቁመዋል፡፡

“በቀጣይ ሁለት .. ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# “የሕዳሴው ግድብ ሥራ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ሉዓላዊ መብት በመሆኑ በድል ታጅቦ ቀጥሏል”

- ኢንጂነር ፈቂ አህመድ ነጋሽ
የሕዳሴው ግድብ ተደራዳሪ ቡድን አባል የነበሩ

ገፅ 4



# ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ለመላው ኢትዮጵያውያን የደስታ መልዕክት አስተላለፉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ የታላቁ ህዳሴ ግደብ 2ተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት በመጀመሩ ለመላው ኢትዮጵያውያን የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት አስተላለፉ፡፡

ግድቡ ኢትዮጵያውያን ተቸግረንና ከመቀነታችን ቀንሰን የገነባነው ነው ያሉት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ፤ አባይ የጠላቶቹን ሟርት ወደ አርት እየቀየረ ፣ አቧራውን አሻራ አድርጎ እነሆ ከ602 ሜትር ከፍታ ላይ ሆኖ እየበረረ ነው ብለዋል።

በታሪክ ውስጥ ማለፍና ታሪክ ሠርቶ ማለፍ የሚባሉ ሁለት ነገሮች አሉ ያሉት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ፤ በታሪክ ውስጥ ማለፍ ዕድል፣ ታሪክ ሠርቶ ማለፍ ግን ዕድልም ድልም ነው፡፡ ይሄ ትውልድ በዓባይ ግድብ ጉዳይ ባለ ዕድልም ባለ ድልም ነው፡፡ የሺ ትውልድ ጥያቄ በሚመለስበት ዘመን ተገኝቶ ግድቡ ሲገደብ በዓይን

ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር
የበረንዳ ታይልስ ኤጋ መደበኛ ኮልሞ
0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565

UNIC ETHIOPIA
ሕብረት ኢንሹራንስ አማ
THE UNITED INSURANCE COMPANY SC
Tomorrows Company Today'
ለህይወት ለሁሉም የመድን ፍላጎትዎ ህጋዊ ግዴታዎ
+251 111 26 34 34
united.insurance@unic-ethiopia.com

# ‹‹የመንግስት ውሳኔ ግድቡ አሁን ለደረሰበት የግንባታ ምዕራፍ እንዲበቃና የኃይል ማመንጨቱ እውን እንዲሆን አስችሏል››

**- ኢንጂነር ኤፍሬም ወልደኪዳን**
**የታላቁ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ምክትል ስራ አስኪያጅ**

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- መንግስት በጥልቀት ገምግሞ ባሳለፋቸው ውሳኔዎች መሰረት በተከታታይነት በተሰሩ ስራዎች ግድቡ አሁን ለደረሰበት የግንባታ ምዕራፍ እንዲደርስና ሩቅ የሚመስለውም የማመንጨት ሂደት እውን እንዲሆን እንዳስቻለው የታላቁ ህዳሴ ግድብ ምክትል ስራ አስኪያጅ ኢንጂነር ኤፍሬም ወልደኪዳን ገለጹ፡፡

ኢንጂነር ኤፍሬም የታላቁ ህዳሴ ግድብ ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት ማብሰሪያ መርሃ ግብርን መሰረት በማድረግ እንደገለጹት፤ የመንግስት ውሳኔ ግንባታው አሁን ለደረሰበት የግንባታ ምዕራፍ እንዲደረስና ሩቅ የሚመስለውም የማመንጨት ሂደት እውን እንዲሆን አስችሏል፡፡

የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ አሁን ላስመዘገበው ውጤት በርካታ ችግሮችን አልፏል፡፡ በተለይም ከ2010 ዓ.ም በፊት በነበረው ሂደት የኤሌክትሪካልና የሃይድሮሊክ እስቲል እስትራክቸር ስራዎች ብዙም ልምዱ ባልነበረው አገር በቀል ኩባንያ እንዲመራ መደረጉ ሥራዎቹን መጎተቱንና አገርንም ለኪሳራ መዳረጉንም አስታውሰዋል፡፡

ሙያው ላይ የበቃ አቅም ተፈጥሮ ባለመገባቱ የተቀመጠውን አላማ ማሳካት እንዳልተቻለ እና በግንባታ ሂደቱ መዘግየት መከሰቱንም ኢንጂነር ኤፍሬም ጠቁመዋል፡፡

የውሃ ሙሌቱን ተከትሎ ከግድቡ ሃይል ማመንጨት የሚያስችለው የኤሌክትሮ ሜካኒካል እና እስቲል እስትራክቸር ስራዎች ተከናውነው ባለፈው የካቲት ወር በአንድ ተርባይን አማካኝነት የመጀመሪያ ዙር ሃይል በይፋ ማመንጨት መጀመሩንም አስታውሰዋል፡፡

‹‹የዩኒት 10 የሃይል ማመንጨት ስራው በየካቲት ወር ጀምሮ እስካሁን እየሰራ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ እስካሁን ከ540 ጊጋ ዋት ሰዓት በላይ ማመንጨት ተችሏል›› ብለዋል፡፡

ከዩኒት 10 ተርባይን ማመንጨት ስኬት በኋላ ሁለተኛውን ማመንጫ ዩኒት 09 ወደ ስራ በማስገባት ኢትዮጵያውያን ከግድቡ የሚያገኙትን የኤሌክትሪክ ሃይል ለማሳደግ ያለረፍት ሲሰራ መቆየቱንና ተግባሩም በስኬት መጠናቀቁን ጠቁመዋል፡፡

ዩኒት 09 ለሃይል ማመንጨት አስፈላጊ መሳሪያዎች ተከላ ተከናውኖ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ቀሪ ስራዎችን የማጠናቀቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ የግንባታ ስራው ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ፍተሻና ሙከራ ስራዎች ተገብቶ ከሐምሌ 30 ቀን ጀምሮ በሙሉ አቅሙ ወደ ትግበራ መግባቱንም አመልክተዋል፡፡

እስካሁን እስከ 250 ሜጋ ዋት ጭኖ የሙከራ ሃይል ማመንጨት ስራ ላይ ይገኛል፡፡ የሃይል ማመንጨት መሰረታዊ ጉዳይን ውሃው የሚንደረደርበት የከፍታ



መጠን እንዲሁም የውሃው ፍሰት መጠን ይወስነዋል፡፡ ሃይሉ ከእነዚህ ሁለት መለኪያዎች ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት አለው ነው ያሉት፡፡

ሙሉ ለሙሉ የግድቡ ግንባታ ከተጠናቀቀ እና የመካከለኛ የግድቡ አካል የከፍታ መጠን እስከ 640 ሜትር ከፍታ በሚደርስበት ጊዜ በሙሉ አቅም 375 ሜጋ ዋት ማመንጨት የሚችሉበት አቅም ደረጃ እንደሚደርስም ጠቁመዋል፡፡

አሁን በተፈጠረለት የከፍታ መጠን እያንዳንዳቸው እስከ 270 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም ይኖራቸዋል ያሉት ኢንጂነር ኤፍሬም፤ ዩኒት 09 እና 10 ብቻ በድምሩ እስከ 540 እና 550 ሜጋ ዋት ድረስ ማመንጨት ይችላሉ ብለዋል፡፡

ይህ ማለት ደግሞ በሁለቱ ተርባይኖች ብቻ፤ የግልገል ጊቤ አንድ፣ የተከዜ እና የአዋሽ መልካሳ ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ተደምረው በሙሉ አቅማቸው ቢሰሩ የሚያመነጩት ሃይል ማለት ነው፡፡ የቀሪ ተርባይኖችን ስራ በማጠናቀቅ ሃይል እንዲያመነጩ ለማስቻልም ስራዎች ተጠናክረው መቀጠላቸውንም ተናግረዋል፡፡

መንግስት ከ2010 ዓ.ም በኋላ የፕሮጀክቱን ሁኔታ በጥልቀት በመገምገም በወቅቱ በአገር ውስጥ ተቋራጮች ተይዘው የነበሩ የስራ ውሎች ተቋርጠው በምትኩ ሙያው እና አቅሙ ባላቸው ኩባንያዎች እንዲሰራ በመደረጉ ለተገኘው ውጤት አስተዋጽኦ ማበርከቱንም ነው የተናገሩት፡፡

ኢንጂነር ኤፍሬም እንደገለጹት፤ ፕሮጀክቱ አሁን ደረጃ ላይ እንዲደርስ እያንዳንዱ ዜጋ፤ በአነስተኛ ስራ ላይ ከተሰማሩ ጀምሮ እስከባለሃብቱ ድረስ በሞራል፣ በሙያ፣ በገንዘብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገውበታል፡፡ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ርብርብ ያደረጉበት ነው፡፡ በዲፕሎማሲውም ከፍተኛ ስራ ተሰርቶበታል፣ የመንግስትም ከፍተኛ ውሳኔ ያረፈበት የኢትዮጵያውያን ፕሮጀክት ነው፡፡




አቶ ጌታነህ ይገዙ



ወይዘሮ ሸዋጌጥ ሰይፈ

ፎቶ፡ ሃዲስ አብርሃ



ወጣት ሶስና አፈወርቅ

# የተርባይኖቹ ኃይል ማመንጨት ለጠላት ሽንፈት

## ለኢትዮጵያውያን ድል መሆኑን ነዋሪዎች ገለጹ

### - ግድቡ እስኪጠናቀቅ ድጋፋቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉም ተናግረዋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የሁለቱ ተርባይኖች ሃይል ማመንጨት ለጠላት ሽንፈት ለኢትዮጵያውያን ደግሞ ትልቅ ድል መሆኑን የአዲስአበባ ነዋሪዎች ገለጹ። ግድቡ እስኪጠናቀቅ የሚያደርጉትን ድጋፍ አጠናክረው እንደሚቀጥሉም ተናግረዋል።

አራት ኪሎ አካባቢ ያገኘናቸው አቶ ጌታነህ ይገዙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፣ የተርባይኖቹ ስራ መጀመር ኢትዮጵያውያን ድል ያገኙበት ብቻ ሳይሆን ጠላቶች ስለኢትዮጵያውያን እንዲያውቁና እንዲረዱ የሚያደርግ ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብም አንድ የሚያደርጉት ጉዳዮች ላይ በአንድነት እንደሚሰራና ለጋራ ጉዳዮች በጋራ እንደሚቆም የሚሳይ መሆኑን የኢትዮጵያ ጠላቶች ሊረዱትና ሊገነዘቡት ይገባል ያሉት አቶ ጌታነህ፣ ያለብንን ውስጣዊ ችግር ፈትተን ካደጉት ሀገራት እኩል የምንሆንበት ጊዜ ቅርብ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝቦች የአንድነት መገለጫ አርማ የሆነው የህዳሴ ግድብ ሁለት ተርባይኖች ኃይል ማመንጨት በመጀመራቸው ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ደስ አላችሁ በማለት ሃሳባቸውን የጀመሩት ደግሞ ወይዘሮ ሸዋጌጥ ሰይፈ ናቸው።

የህዳሴው ግድብ የሁላችንም አሻራ ያረፈበት፣ ከጨለማ የሚያወጣን የጋራ ብሄራዊ ሀብታችንና የጥንካሬያችን መገለጫ ነው ያሉት ወይዘሮ ሸዋጌጥ፤ እኛ ኢትዮጵያውያን ያለማንም ጣልቃ ገብነት በራሳችን ጉልበት፤ በራሳችን የሰው ሃይል እራሳችንን ችለን እዚህ በመድረሳችን እጅግ ልኮራ ይገባል ብለዋል።

የህዳሴ ግድቡ የሁሉም ኢትዮጵያውያን አሻራ ያረፈበት ፕሮጀክት እንደመሆኑ መጠን በቀጣይም ሕዝቡ የፕሮጀክቱን ቀሪ ስራ ለማጠናቀቅ የተጀመረውን ተሳትፎ አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አሳስበዋል።

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁለት ተርባይኖች ኃይል ማመንጨት በመጀመራቸው መደሰታቸውን የገለጸው ደግሞ ወጣት ተስፋዬ ብርሃኑ ነው።

ሁለቱ ተርባይኖች ሃይል ማመንጨት መጀመራቸው መብራት የማያገኙ አካባቢዎች መብራት የሚያገኙበት ጊዜ ሩቅ አለመሆኑን የሚያመለክት ነው ያለው ወጣት ተስፋዬ፣ ሀገራችን በኢኮኖሚ፣ በማሕበራዊና በፖለቲካዊ መስኮች ለውጥ እንድታመጣ ያስችላታል ብሏል።

የኢትዮጵያ ጠላቶች አላስፈላጊ የሆኑ ድርጊቶቻቸውን ትተው ሰላማዊ በሆነ መንገድ ችግሩን ለመፍታት መሞከር ይኖርባቸውል ያለው ወጣ ተስፋዬ፤ ከዚህ ውጪ የሚደረግ ድርጊት ከጠቀሜታው ይልቅ ጉዳቱ ይበልጣል ሲልም ተናግሯል። ኢትዮጵያ ግን በሁሉም አማራጮች አሸናፊ እንደምትሆን ሊገነዘቡት እንደሚገባም አሳስቧል።

ሌላው አስተያየት ሰጪ አቶ አያሌው አሰፋ በበኩላቸው፣ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ውስብስብ ችግሮችን አልፎ ኃይል ማመንጨት መጀመሩ ኢትዮጵያውያን በአንድነት የማንሻገረው ችግር እንደሌለ ማሳያ ነው ብለዋል። ሕፃን አዋቂ ሳይል ሁሉም ያለውን አውጥቶ ያስገነባው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ለዚህ ደረጃ መብቃቱ የሚያኮራ ተግባር መሆኑንም ገልጸዋል። “እኛ ኢትዮጵያውያን በራሳችን ማንኛውንም ልማት እውን ማድረግ እንደምንችል ከዓድዋ ድል ቀጥሎ ታላቁ ህዳሴ ግድብ ህያው ምስክራችን በመሆኑ ኮርቻለሁ” ብለዋል።

የግድቡ ሁለት ተርባይኞች ኃይል ማመንጨት ከመጀመራቸውም በላይ አንድነታችንን ለማጠናከር፣ ብሄራዊ መግባባት ለመፍጠርና ሀገርን በጋራ ለማልማት ትልቅ አቅም ይሆነናል ብለዋል።

ወጣት ሶስና አፈወርቅ በበኩሏ፣ የህዳሴው ግድብ ሁለት ተርባይኖች ኃይል ማመንጨት መቻላቸው ሀገራዊ ዲፕሎማሲውን ለማጠናከር፣ የውጭ ጫናውን ለማቃለልና አንድነታችንን ለማጠናከር ያግዛል ብላለች።

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በተለይም ለወጣቱ ዘርፈ ብዙ ተስፋዎችን የሰነቀ የኢኮኖሚ መሰረታችን በመሆኑና ለፍሬ መብቃቱ ድርብ ደስታ መሆኑን ገልጻለች።

የግድቡን ግንባታ ለማስተጓጎል ተባብረው ይሰሩ የነበሩ አንዳንድ የውስጥና የውጭ ኃሎችን ያሳፈረ፤ ወዳጆቻችንን ደግሞ ደስታ ያጎናፀፈ ልዩ ቀን ነው ስትልም ተናግራለች።

የህዳሴ ግድብ ከዚህ ደረጃ ለመድረሱ ዋነኛው ሚስጥር የኢትዮጵያ ሕዝቦች በአንድነት መቆም ነው” ያሉት አቶ ዘላለም ምሬሳይ፣ ግድቡ እስኪጠናቀቅ ሕብረተሰቡ ድጋፉን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባው ገልጸዋል።

የህዳሴ ግድቡ ሙሉ በሙሉ እስኪጠናቀቅ የጀመሩትን ድጋፍ አጠናክረው እንደሚቀጥሉም ነዋሪዎቹ ተናግረዋል።

# የግድቡ ግንባታ እስከሚጠናቀቅ ሁሉን አቀፍ ርብርብ እንዲቀጥል የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጥሪ አቀረበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የህዳሴ ግድብ ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት መጀመሩ ኢትዮጵያውያን በአንድነት በሁሉም መስክ እያደረጉ ባሉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በመሆኑ አሁንም የግድቡ ግንባታ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ሁሉን አቀፍ ርብርብ መቀጠል ይኖርበታል ሲል የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት መጀመሩን ምክንያት በማድረግ ትናንት “የህዳሴ ግድብ ለኢትዮጵያዊያን መብራትም እራትም ነው!”በሚል በሰጠው መግለጫ እንዳለው፤ የህዳሴ ግድብ ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት መጀመሩ ኢትዮጵያውያን በአንድነት በሁሉም መስክ እያደረጉ ባሉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ነው፡፡ አሁንም የግድቡ ግንባታ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ሁሉን አቀፍ ርብርብ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት ጀምሯል። ይህ ታላቅ የምስራች ነው። ይህም ከወራት በፊት የተጀመረውን ኃይል የማመንጨት አቅም በማሳደግ የግድቡን ግንባታ ወደላቀ ደረጃ የሚያሸጋግር ነው ያለው የመቻል አቅማችንን የሚያሳይ፣ የልማት ፍላጎታችንን የሚያመላክት፣ የህብረት ስኬታችንን በጉልህ የሚያሳይ ፕሮጀክት መሆኑን አመልክቷል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ የግድቡ ግንባታ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ ያልተቋረጠ ድጋፍ እያደረገ ነው ያለው መግለጫው፤ የህዳሴ ግድብ ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት ላይ የተደረሰው ኢትዮጵያውያን በአንድነት በሁሉም መስክ እያደረጉ ባሉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በመሆኑ አሁንም የግድቡ ግንባታ እስከሚጠናቀቅ ድረስም ሁሉን አቀፍ ርብርብ መቀጠል ይኖርበታል ብሏል፡፡

የኢትዮጵያ ልጆች በአንድነት ተባብረው የህዳሴውን ግድብ በማጠናቀቅ ለአፍሪካ ተምሳሌት መሆናቸውን በተግባር እንደሚያሳዩ የእስካሁኑ ስኬት ትልቅ ማሳያ መሆኑን መግለጫው አመልክቶ፤ ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቷን ተጠቅማ የኤሌክትሪክ ኃይል ስታመነጭ በሚሊየን ለሚቆጠሩ ዜጎች የልማት ስንቅ ከመሆኑም ባሻገር ለተቀሩት አፍሪካውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ደግሞ የልማት ተነሳሽነትን እንደሚፈጥር መግለጫው አስታውቋል፡፡

በማገዶ እንጨት መሸከም ወገባቸው የጎበጠ እናቶቻችን እና እህቶቻችንን ቀና አድርጎ መብራት እና እራት እንደሚሆን መግለጫው ጠቁሞ፤ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በኢትዮጵያ ልጆች የህብረት ስራና ቁርጠኝነት እንዲጠናቀቅ አሁንም ሁለተናዊ ድጋፉ ተጠናክሮ መቀጥል እንደሚኖርበት አስታውቋል፡፡

# ሚኒስቴሩ ከ70 ሺህ በላይ የውጭ አገራት ዜጎች መመዝገባቸውን አስታወቀ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- በሕገወጥ መንገድ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ከ70 ሺህ በላይ የውጭ አገራት ዜጎች መመዝገባቸውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ አለም ትናንትና በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያ የውጭ አገራት ዜጎች ወደ ሕጋዊ ስርዓት እንዲገቡ የሚረዳ ምዝገባ እያከናወነች ይገኛል። ከተለያዩ አገራት የመጡ ከ70 ሺህ በላይ ሰዎች ተመዝግበዋል።

እንደ አምባሳደር አለም ገለጻ፤ በእስካሁኑ ምዝገባ በተለያዩ መንገድ ወደኢትዮጵያ የገቡ ከካናዳ፣ ከአሜሪካ፣ ከጣሊያን፣ ከኮንጎ፣ ከናይጀሪያ፣ ከየመን፣ ከሶሪያ፣ ከሱዳን፣ ከደቡብ ሱዳን፣ ከቻይና፣ ከኤርትራ፣ ከቡሩንዲ፣ ከጋና፣ ከባንግላዴሽ፣ ከሕንድ፣ ከላይቤሪያ፣ ከካሜሮን የመጡ ዜጎች ተገኝተዋል።

በህገወጥ መንገድ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ የውጭ ሀገራት ዜጎችን ሕጋዊ የማድረግ ምዝገባው የተጀመረው ሐምሌ 11 ቀን 2014 ዓ.ም እንደነበር ያስታወሱት ቃል አቀባዩ፤ ምዝገባው እስከ ነሐሴ 13 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ እንደሚቆይ ጠቁመዋል።

የምዝገባ ጊዜ ገደቡን አልፈው የተገኙ የውጭ አገራት ዜጎች ላይ መንግሥት ዓለም አቀፍ ሕግጋትን በተከተለ መንገድ ሕጋዊ ርምጃ እንደሚወስድ አሳስበዋል።

በተለያዩ የቪዛ ዓይነት ወደ ኢትዮጵያ የገቡና ቪዛቸው የሚፀናበት ጊዜ ያለፈበት፤ የመኖሪያ ፈቃዳቸው የሚፀናበት ጊዜ ያለፈበት፤ ምንም አይነት ቪዛም ሆነ የመኖሪያ ፈቃድ የሌላቸው የውጭ አገራት ዜጎች ምዝገባው የሚመለከታቸው መሆኑን ገልጸዋል።

በተጨማሪም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የስደተኞችና ተመላሾች



ፎቶ - ዳኜ አበራ

አምባሳደር መለስ አለም

አገልግሎት የስደተኝነት ወይም የጥገኝነት ጠያቂ ዕውቅና አግኝተው በከተማ ስደተኝነት ለመኖር የተፈቀደላቸው፣ያለፈቃድ ከተለያየ የስደተኛ ጣቢያ በመምጣት የሚኖሩ የውጭ ዜጐችም ምዝገባውን ማከናወን እንደሚጠበቅባቸው ቃል አቀባዩ አስታውቀዋል።

በሌላ በኩል መንግሥት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተፈጠረው ግጭት ፖለቲካዊ መፍትሄ እንዲያገኝ ለማድረግ ለሰላም ውይይቱ ቁርጠኛ መሆኑን በተመለከተ ያነሱት ቃል አቀባዩ፤ የኢትዮጵያ መንግስት ልክ እንደ ሕዳሴ ግድብ ሁሉ የአፍሪካ ችግር በአፍሪካ መፈታት አለበት የሚል ጽኑ አቋም አለው ብለዋል።

የመንግሥት አቋም በአፍሪካ ሕብረት መሪነት የተጀመረው የሰላም ጥረት እንዲቀጥል ነው። ሌላ ምንም አይነት ተመሳሳይ /parallel/ ጥረት ተቀባይነት የለውም ሲሉ ገልጸዋል።

የአፍሪካ ህብረት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ የቀድሞው የናይጄሪያ ፕሬዚዳንት ኦሊሴንጎ ኦባሳንጆ በሰላም ውይይቱ አመቻችነት እንዲቀጥሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ፍላጎት ነው። አስፈላጊ ከሆነ በአፍሪካ ሕብረት አማካኝነት ፕሬዚዳንት ኦባሳንጆን የሚደግፉ የአፍሪካ ታዋቂ ሰዎች ቢጨመሩ ኢትዮጵያ አትቃወምም ሲሉ የመንግሥትን አቋም አሳውቀዋል።

በትግራይ የመሰረታዊ አገልግሎት መጀመርን ለሰላማዊ ውይይቱ መንግስት በቅድመ ሁኔታነት አያስቀምጥም፡፡ ሆኖም አገልግሎቶቹን ለማስጀመር ምክክር እና ዝርዝር ውይይት ማድረግ ያስፈልጋል። የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አካላት የገንዘብ፣ የተቴክኒክና የሎጂስቲክስ ድጋፍ እንዲያደርጉ ይበረታታል ብለዋል።

ስለታላቁ የኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብ ያነሱት አምባሳደር መለስ፤ ከሰሞኑ በሱዳንና በግብጽ አካባቢዎች ጎርፍ መከሰቱን በማስታወስ የጎርፍ ተጽዕኖው መከሰቱ የህዳሴው ግድብ ግንባታ ቢከናወንም በአገራቱ የውሃ አቅርቦት ላይ ጉዳት እንደማያደርስ ያሳየ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ቃል አቀባዩ ገለጻ፤ የህዳሴው ግድብ የታችኞቹ ተፋሰስ አገራትን የሚጠቅምና ዓለም አቀፍ የግንባታ ደረጃዎችን የተከተለ ፕሮጀክት ነው። ኢትዮጵያም ለቀጣናው ኢኮኖሚያዊ ትስስር ጠቀሜታ ያለውን ፕሮጀክት በመገንባት የተፈጥሮ ሃብቷን የማልማት መብቷን እየተጠቀመች ነው።

## ርዕሳነ-መስተዳድሮች የግድቡ ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨትን አስመልክቶ የእንኳን ደስ አለን መልዕክት አስተላለፉ

**ሙሳ ሙሀመድ**

አዲስ አበባ፡- ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት መጀመሩን አስመልክቶ ክልል ርዕሳነ-መስተዳድሮች የእንኳን ደስአለን መልዕክታቸውን ለመላው ኢትዮጵያውያን አስተላልፈዋል፡፡

የጋምቤላ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኡሞድ ኡጁሉ፣ የሀረሪ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድርና በክልሉ የታላቁ ህዳሴው ግድብ ማስተባበሪያ ምክር ቤት ሰብሳቢ ወይዘሮ ሚስራ አብደላ፣ የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አወል አርባ፣ የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ከድር ጁሃር፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፣ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁለተኛ ተርባይን የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት መጀመሩ የአሸናፊነታችን አርማና የአንድነታችን ውጤት መሆኑን በመግለጽ ለመላው ኢትዮጵያውያንና ለክልሉ ሕዝብ የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ውስብስብ ችግሮችን አልፎ ኃይል ማመንጨት መጀመሩ ኢትዮጵያውያን በአንድነት ከቆምን የማንሻገረው ችግር እንደሌለ ተጨባጭ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡ ሕፃን አዋቂ ሳይል ሁሉም ያለውን አዋጥቶ ያስገነባው ታላቁ ግድብ ለእዚህ ደረጃ መብቃቱ የሚያኮራ ተግባር መሆኑንም ገልጸዋል። ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት መጀመሩ ግድቡ የሁላችንንም አሻራ ያረፈበት፣ ከጨለማ የሚያወጣን የጋራ ብሔራዊ ሀብታችን መሆኑንም አሳይቷል። ግድቡ ኃይል ከመስጠቱና የዘመናት ችግራችን መፍታት ከመጀመሩም በላይ አንድነታችንን ለማጠናከር፣ ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠርና በጋራ ማልማት እንደምንችልም አስተምሮናል ብለዋል።

የህዳሴ ግድቡ ውስጣዊና ውጫዊ ጫናዎችን በብርቱ ተቋቁሞ ኃይል ማመንጨት መጀመሩ ሃገራዊ ዲፕሎማሲውን ለማጠናከር፣ የውጭ ጫናውን ለማቃለልና አንድነታችንን ለማጠናከር እንደሚያግዝም ገልጸዋል። የግድቡ ቀሪ የኃይል ማመንጫ ስራዎች ተጠናቀው ሙሉ በሙሉ አገልግሎት እንዲሰጡ እያደረጉት ያለውን ድጋፍ ክልሉና ከተማ አስተዳደሩ አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ተናግረው፤ የግድቡ ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት በመጀመሩ ለመላ ኢትዮጵያውያን እንኳን ደስ አላችሁ ሲሉ መልዕከታቸውን አስተላልፈዋል። ኢትዮጵያውያን በፕሮጀክቱ ላይ ያሳዩት ጥረትና አንድነት ፍሬ ማፍራት መጀመሩን ያሳየ ነው ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ሃገሪቱ በበርካታ ፈተናዎች ውስጥም ሆና የታላቁ ህዳሴው ግድብ ሁለተኛው ተርባይን ኃይል እንዲያመነጭ ማስቻሏ ሕዝብና መንግስት ቁርጠኛ ከሆኑ ፈተናዎችን በመቋቋም ውጤታማ መሆን እንደሚቻል የሚያመላክት ነው ሲሉ ተናግረዋል። ይህ ታላቅ ውጤት እንዲገኝ ላደረጉ ባለሙያዎች፣ የፀጥታ አካላት፣ አመራሮች፣ በተለይም ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ምስጋና አቅርበው ግድቡ ሙሉ በሙሉ እስኪጠናቀቅ ሕዝቡ ድጋፉን እንዲያጠናክር ጠይቀዋል።

የልባችን ሙላት ፣ የአንድነታችን ማሰሪያ ፣ የኢትዮጵያዊነታችን አርማ ፣ የሩቅ ትልማችን ወኔና ጉልበት ፣ የመለወጥ ዘመናችን ማብሰሪያ የሆነው የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁለተኛ ተርባይን ኃይል ማመንጨት በመጀመሩ ሁላችሁም እንኳን አደረሳችሁ ብለዋል፡፡

የአማራ ክልል ርእሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ በበኩላቸው፤ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ሁለተኛው የኃይል ማመንጫ ዩኒት በይፋ ኃይል ማመንጨት ጀምሯል። ይህ የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ድል፤ የመደጋገፍና አንድነት ውጤት ነው። በአንድነት ከቆምን ለስኬት እንደምንበቃ ማረጋገጫ ነው ብለዋል።

ከሁሉም በላይ የጋራ ጠላት የሆነውን ድህነት ማሸነፍ የምንችለው ያለንን የተፈጥሮ ፀጋ በጋራ አልምተን በአግባቡ መጠቀም ስንችል መሆኑን መረዳት ይገባል ያሉት ዶክተር ይልቃል፤ ከተባበርንና ከተደጋገፍን ዳር የማናደርሰው የልማት ተግባር የለም፤ ለዚህ ደግሞ ታላቁ የህዳሴ ግድብ አንዱ ማሳያ በመሆኑ ግድቡ እውን እንዲሆን በተደረገው ሁለንተናዊ ተሳትፎ የበኩላችሁን ለተወጣችሁ መላ ኢትዮጵያውያን እንኳን ደስ አላችሁ፤ እንኳን ደስ አለን ሲሉ ገልጸዋል።



# ምክር ቤቶቹ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክት አስተላለፉ

**ሙሳ ሙሀመድ**

አዲስ አበባ፡- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች የግድቡ ሁለተኛ ዩኒት ኃይል ማመንጨት በመጀመሩ የተሰማቸውን ደስታ በመግለጽ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክት አስተላለፉ፡፡

ታላቁየህዳሴግድብየሁሉምኢትዮጵያውያን አሻራ ያረፈበት፣ ከፍተኛ የገንዘብ እና ዘርፈ-ብዙ መስዋዕትነት የተከፈለበት ትልቅ አገራዊ ውጤት ነው ያለው የምክር ቤቱ መግለጫ፣ ግድቡ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ያረጋገጠ ዘመን ተሻጋሪ ቅርስም ነው ሲል አስነብቧል፡፡

ምክር ቤቱ አገራዊ ትብብራችን እና አንድነታችን በሁሉም ዘርፎች ተጠናክሮ እንዲቀጥልም ጥሪውን አስተላልፏል፡፡

በተመሳሳይም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤ የተከበሩ አቶ አገኘሁ ተሻገር የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የጋራ አርማ የሆነው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁለተኛው ተርባይን ተጨማሪ ኃይል ማመንጨት በመጀመሩ የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# “የሕዳሴው ግድብ ሥራ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ሉዓላዊ መብት በመሆኑ በድል ታጅቦ ቀጥሏል”

\- ኢንጂነር ፈቂ አህመድ ነጋሽ
የሕዳሴው ግድብ ተደራዳሪ ቡድን አባል የነበሩ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ለዕኩይ ዓላማቸው ድጋፍ ለማሰባሰብ ቢንቀሳቀሱም የግድቡ ሥራ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ሉአላዊ መብት በመሆኑ በድል ታጅቦ መቀጠሉን ኢንጂነር ፈቂ አህመድ ነጋሽ ገለጹ፡፡

የሕዳሴው ግድብ ተደራዳሪ ቡድን አባል የነበሩት ኢንጂነር ፈቂ አህመድ ነጋሽ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ሙሌት ከመካሄዱ በፊት ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያሰሙ ነው የቆዩት፡፡ ጉዳዩን ወደ ጸጥታው ምክር ቤት በመውሰድና ድጋፎችን በማሰባሰብ የግድቡን ሥራም ሆነ ሙሌት ለማደናቀፍ ሲሠሩ ነበር፡፡ ሆኖም የግድቡ ሥራ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ሉአላዊ መብት በመሆኑ በድል ታጅቦ ቀጥሏል፡፡

የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ከፍተኛ ጉዳት ያደርስብናል በሚል የሕዳሴው ግድብ ግንባታንም ሆነ የግድቡን ሙሌት ወደ ጸጥታው ምክር ቤት ሲወስዱ መቆየታቸውን የጠቀሱት ኢንጂነር ፈቂ አህመድ፤ ጉዳዩን ዓለም አቀፍ ስጋት ለማስመሰልም እንቅስቃሴ ሲያደርጉ መቆየታቸውና በተለይም ግብፅ የአባል ሀገራቱን ስምምነት በሚጥስ መልኩ አሁንም ጉዳዩን ወደ ጸጥታው ምክር ቤት እየወሰደች እንደምትገኝ ተናግረዋል፡፡

ሆኖም አሁን ኢትዮጵያ በሕዳሴ ግድቧ የምትይዘው ውሃ በታችኛው የውሃው ተፋሰስ ሀገራት ላይ ጉዳት እንደማያደርስ የሚያረጋግጥና በጋራ ከሀገራቱ ጋር በመመካከር መስራት እንደሚቻል ነው የገለጹት፡፡



የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ሕዝባቸውን በአሉባልታ ሲያደናግሩ ስለቆዩ ግድቡ ከሞላ በኋላ ጉዳት ሳያደርስ ሲቀር በሕዝባቸው ትዝብት ውስጥ ላለመግባት በሌላ መንገድ ሊቀጥሉ ይችላሉ ያሉት ኢንጂነሩ፤ የዚህ ግዙፍ ግድብ ትልቁ ተግባር ኃይል ማመንጨት በመሆኑ ስጋት ውስጥ ሊከታቸው እንደማይገባ አብራርተዋል፡፡

እንደ ኢንጂነር ፈቂ አህመድ ገለፃ፤ ሀገራት በድንበር ተሻጋሪ ወንዞቻቸው አለመግባባትና መፋጠጥ ላይ ይደርሳሉ፤ መጨረሻ ላይ ግን ወደ ትብብርና ወደ ስምምነት ነው የሚሄዱት፡፡ በቅርቡ ግብፅ የሀገራቱን ስምምነት ጥሳ ወደ ጸጥታው ምክር ቤት የወሰደችውን ጉዳይ አሁንም ምክር ቤቱ እንደተለመደው ወደ አፍሪካ ሕብረት ይመልሰዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ያም ሆኖ በኢትዮጵያ ደረጃ ብዙ የዲፕሎማሲና የተግባቦት ሥራዎች መሠራት አለባቸው፡፡

በኢትዮጵያ በኩል በንቃት ሊሠሩ ይገባል ያሏቸውን ጉዳዮችም ኢንጂነሩ ተናግረዋል፡፡ በተለይም ግብፅ ወደ ጸጥታው ምክር ቤት የላከችውን ክስ አስመልክቶ ወደ ተለያዩ ሀገራት በመሄድና የኢትዮጵያን አቋም በማሳወቅ ድጋፍ የሚገኝባቸው ሁኔታዎች ላይ ብዙ መሠራት ያለባቸው ሥራዎች አሉ ብለዋል፡፡

በተግባቦትና ዲፕሎማሲ ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት ግብፅ ወደ ጸጥታው ምክር ቤት የወሰደችውን የሕዳሴው ግድብን ጉዳይ ወደ አፍሪካ ሕብረት ማስመለስ ይቻላል የሚል እምነት እንዳላቸውም አክለው ገልጸዋል፡፡

ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ በተጎሳቆለ አኗኗር ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ሕይወት እንደሚቀይርም አንስተዋል፡፡ ከግድቡ የሚገኘው የኤሌክትሪክ ኃይል በሀገር ውስጥ እና ለውጭ ሀገራት ተሸጦ ከፍተኛ ገቢ እንደሚያስገኝና የኢንዱስትሪዎችን የኃይል ፍላጎት እና የውሃና ጤና ተቋማትን ፍላጎት በማሟላት የሀገሪቱን ዕድገት ከፍ እንደሚያደርግ ብሎም በየቤተሰቡ ውስጥ የኑሮ መሻሻልን የሚፈጥር መሆኑን ኢንጅነሩ አብራርተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት የሕዳሴ ግድብ ሁለተኛ ተርባይን ኃይል ማመንጨት መጀመር ማብሰሪያ ሥነ ሥርዓት በትናንትናው ዕለት ተከናውኗል፡፡

## “በቀጣይ ሁለት ተኩል...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የታላቁ ኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁለተኛ ተርባይን ኃይል ማመንጨት ማብሰሪያ ሥነ ሥርዓት ትናንት በጉባ በተካሄደበት ወቅት የታላቁ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ዋና ስራ አስኪያጅ ኢንጂነር ክፍሌ ሆሮ፤ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በ2014ዓ.ም ለማከናወን ከተያዙት አበይት እቅዶች መካከል በሁለት ተርባይነሮችና ጀኔሬተሮች ኃይል ማመንጨት አንዱ መሆኑን ጠቅሰው፤ እቅዱ ተሳክቶ በሁለቱም ዩኒቶች ኃይል ማመንጨት እንደተቻለ ገልጸዋል፡፡ በቀጣይ ሁለት ተኩል ዓመታት ጊዜ ውስጥም ግድቡን ሙሉ ለሙሉ ለማጠናቀቅ ታስቦ እየተሰራ እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡

ኢንጂነር ክፍሌ እንደገለጹት፤ ከለውጡ በኋላ በፕሮጀክቱ ላይ የማስተካከያ እርምጃ ከተወሰደ ወዲህ በሦስት ዓመታት ውስጥ በግድቡ ውስጥ መተከል የነበረባቸውን የውሃ ማስተላለፊያ የብረታ ብረት ሥራዎችን በማጠናቀቅ የመካከለኛውን የግድብ ከፍታ ከ25 ሜትር ወደ 100 ሜትር ማድረስ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የግድቡን ግራና ቀኝ በትንሹ እስከ 645 ሜትር ማድረስ ተችሏል፡፡ ከባህር ጠለል በላይ እስከ 645 ወይም 145 ሜትር ከመሠረት ከፍ ያለ፤ እንዲሁም በትንሹ እስከ 111 ሜትር ከፍ በማድረግ ሁለት ሙሌቶችን ማከናወን የተቻለ ሲሆን፤ ሦስተኛው ሙሌት በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

ከምንም ደረጃ ተነስቶ ሁለት ተርባይነሮችና ጀኔሬተሮች በመትከል ኃይል ማመንጨት ተችሏል ያሉት ኢንጂነሩ፤ የሲቪል ስራዎች ግንባታ ወደ 95 በመቶ፣ የኤሌክትሮ ሜካኒካል ፍብረካና ተከላ ሥራ ወደ 61 በመቶ ከፍ በማድረግ እንዲሁም የውሃ ማስተላለፊያ የብረታ ብረት ሥራዎችን ወደ 73 በመቶ በማድረስ ዛሬ ላይ የፕሮጀክቱን አፈጻጸም 83 ነጥብ ሦስት በመቶ ለማድረስ እንደተቻለ ገልጸዋል፡፡

በቀጣይ ሁለት ተኩል ዓመታት ውስጥ ግድቡን ሙሉ ለሙሉ በማጠናቀቅ በየደረጃው ሙሌት በማከናወን ቀሪ ዩኒቶችን በመትከል ኃይል በማመንጨት ፕሮጀክቱን ለማጠናቀቅ ታስቦ እየተሰራ እንዳለም ኢንጂነር ክፍሌ ተናግረዋል፡፡

ኢንጂነር ክፍሌ፤ “ባለፉት ሁለት ዓመታት ከምንጊዜም በላይ አገራችን ከውስጥና ከውጭ የተፈተነችበት፤ እንዲሁም ፕሮጀክቱን ለማሰናከል ከፍተኛ ርብርብ የተደረገበት ወቅት ቢሆንም፤ በመንግስት ሙሉ ድጋፍና ክትትል ፈተናዎችን ሙሉ በሙሉ በማለፍ የፕሮጀክቱ ግንባታ ሳይስተጓጎል በሚያስደንቅ ሁኔታ ከጠላቶቻችን ጭምር ከፍተኛ አድናቆት የተቸረው ሆኖ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ደርሷል” ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ፕሮጀክቱን ምንጊዜም በመደገፍና አመራር በመስጠት ከጎናቸው ላልተለዩ፤ በተገኘው ውጤት ሳይኩራሩ ለተጨማሪ ግብ እንዲሰሩ ለሚያተጓቸው ለጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና ለምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን እንዲሁም ለሌሎች ከፍተኛ የአመራር አካላት ምስጋና አቅርበዋል፡፡

## “ታላቁ የኢትዮጵያ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የታሰበውን ግድብ ከሃሳብ ወደ ተግባር፣ ከመገደብና ከበርካታ ፈተናዎች ውስጥ አልፎ በዚህ ወቅት ሁለተኛውን ዩኒት ኃይል ማመንጨት ወደሚችልበት ደረጃ ማድረስ መቻላችን ተረት የነበረውን ታሪክ ማድረጋችንን ያሳያል ብለዋል፡፡

ከዚህም አልፎ አይቻልም የተባለውን ተችሎ በማየታችን እንደ ዜጎች የምንኮራ ሲሆን፤ ከዚህ በላይ ግን የአባቶቻችንን ትልምና ፍላጎት በማሳካት ሀገራችንን በፀና መሰረት ላይ ማቆም የዚህ ትውልድ ዋነኛ ኃላፊነት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን የፀናችና የበለፀገች ሀገር ማቆየት ከቻልን ሀገሪቱ ባፈራችው ሀብት ትውልድ የሚጠቀም በመሆኑ ሀገርን የማፅናትና የማበልፀግ ጥረት ውስጥ አቅም በፈቀደ ሁሉ ተሳታፊ መሆን ከሁሉም ዜጎች የሚጠበቅ ይሆናል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩል ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን በተመለከተ የታችኞቹ ተፋሰስ ሀገራት በተለይም ሱዳንና ግብፅ ኢትዮጵያ ኃይል በማመንጨት ኢኮኖሚዋን ማሻሻል፣ በጭለማ ውስጥ የሚኖሩ ዜጎችን ብርሃን እንዲያገኙ ከመፈለግ ውጪ ሀገራቱን የመጉዳት ዓላማ እንደሌላት በተደጋጋሚ ስትገልጽ መቆየቷንም አውስተዋል፡፡

በዚህ ዓመት ሶስተኛውን የውሃ ሙሌት ያረጋገጠው 22 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ገደማ ውሃ መያዝ የሚችል ስራ እንዲሁም ሁለት ዩኒት ማመንጨት የሚችል ስራ ሲሰራ የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ላይ ምንም አይነት የውሃ እጥረት እንዳያጋጥምና ውሃው ኃይል እያመነጨን አንድም ቀን ሳይቋረጥ እንዲሄድ የተደረገ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም የታችኞቹ ተፋሰስ ሀገራት ይህን እውነታ በመገንዘብ በስምምነት ውስጥ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ከልብ በማመን ለዚህም እንዲተጉ ገልጸው፤ ከዚህ ውጪ ያለው ማንኛውም አማራጭ የጀመርነውን ስራ የማያስቆም መሆኑን ተገንዝበው ወደ ሰላም፣ ወደ ድርድርና በጋራ ወደማደግ እንዲመጡ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አሁን ያለበት ደረጃ የሚያሳየው የኢትዮጵያ ብልፅግና እውን የሚሆንና ማንም ሊያስቆመው እንደማይችል ተናግረው፤ በወቅቱ በመከወን፣ በብቃት በመጨረስ፣ ወደሚቀጥለው ደረጃ የሚያድግ መሆኑን ማሳያ እንደሆነም አመላክተዋል፡፡

የአመቱን እቅድ ከአስር ቀን በፊት ቀድሞ መከወን የተቻለው በብዙ ኢትዮጵያውያን ዜጎች ጥረት በመሆኑ ያሰብነውን ማሳካት ብቻ ሳይሆን ቀድመን ማሳካት መቻላችንን ያሳየ ነው ብለዋል፡፡ በመሆኑም መላው ኢትዮጵያውያን ወደ ብልጽግና ለሚደረገው ጉዞ የራሳቸውን አሻራ እንዲያስቀምጡ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በዚህ ስራ ውስጥ በገንዘባቸው፣ በዕውቀታቸው እንዲሁም በቦታው በመገኘት ስራው ቢታቀደለት መሰረት እንዲከወን ጥረት ያደረጉ አካላትንም አመስግነዋል፡፡

# ብልጽግና ፓርቲ ሁለተኛው ተርባይን ኃይል በማመንጨቱ ለመላው ኢትዮጵያውያን የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት አስተላለፈ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ብልጽግና ፓርቲ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁለተኛ ተርባይን ሃይል ማመንጨት በመጀመሩ ለመላ ኢትዮጵያውያን የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት አስተላለፈ፡፡

ፓርቲው ፤ የኢትዮጵያዊነታችን ዓርማ የጋራ ጥረታችን አሻራ የሆነው ታላቁ የህዳሴ ግድባችን ሁለተኛ ተርባይን ሃይል ላመነጨበት ለዚህ ታሪካዊ ቀን እንኳን አደረሳችሁ ብሏል።

“ስለኢትዮጵያችን ብልጽግና የጋራ ራዕይ ሰንቀን በጋራ ጀመርን፣ ውጣ ውረዱን ሁሉ በጋራ ተጋፈጥን፤ ያሰብነውን ከማሳካት ማንም እንደማያስቆመን በተግባር አሳየን” ሲልም በማህበራዊ ትስስር ገጹ መልዕክቱን አጋርቷል።

እኛ ኢትዮጵያውያን ለጋራ ዓላማ በአንድነት ከቆምን ማንኛውንም ፈተና አሸንፈን በድል እንደምንሻገር ታላቁ የህዳሴ ግድባችን ህያው ምስክራችን ነው ሲልም ነው ፓርቲው የገለጸው።

ኢትዮጵያውያን ሁሉ ፕሮጀክቱ ለዛሬው ስኬት እንዲበቃ በገንዘብ፣ በእውቀት፣ በጉልበትና በሃሳብ አሻራ ማኖራቸውን የገለጸው ፓርቲው፤ እንኳን የልፋታችሁን ዋጋ ለማየት በቃችሁ ብሏል፡፡

ታላቁ የህዳሴ ግድብ የኢትዮጵያውያን ሁሉ የጋራ ሀብት ብቻ ሳይሆን የሉዓላዊነታችንና የሀገራዊ ክብራችን መገለጫ አርማ ነው፤ ልፋታችሁ ፍሬ እያፈራ ይቀጥላልም ብሏል በመግለጫው፡፡ የዛሬው ስኬትና ድል የኤሌክትሪክ ሃይል ብቻ ሳይሆን የአንድነትን ሃይል ይጨምራል ሲልም ገልጿል።

የሕዳሴን ፕሮጀክት በአጭር ጊዜ አጠናቀን በህብረ ብሔራዊ አንድነት በስኬት ጎዳና እንደምንገሰግስ በዛሬው ድል አረጋግጠናል ያለው ፓርቲው ፤ ፈተናዎችን ሁሉ በጋራ እያሸነፍን እንሻገራለን ፤ የኢትዮጵያን ብልጽግናም እውን እናደርጋለን ሲልም መልዕክት አስተላልፏል።

## ፕሬዚዳንት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ማየት፣ በእጅ መዳሰስ፣ በእግር መርገጥ ባለ ዕድል ሲያደርግ፤ ለግንባታው ገንዘባቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ጉልበታቸውን ከለገሡት፣ በዲፕሎማሲና በሚዲያ ለዓባይ ከሚከራከሩት፣ ታሪክ ሠሪ ጀግኖች ወገን መሆን ደግሞ ባለ ድል ያድርጋል ሲሉም የጠቅላይ ሚኒስትሩን ንግግር ተጋርተዋል፡፡

ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ በመልዕክታቸው፤ «እነሆ አሁን የሕዳሴ ግድብ ከንድፍ አልፎ፣ ግንባታው ተገባዶ፣ ግዙፍ ውሃ በጉያው ይዞ ኃይል ማመንጨት ጀምሯል። ዛሬ ዓባይ ተረት ሳይሆን የሚጨበጥ እውነት ነው፤ ከዘፈንና እንጉርጉሮ ወጥቶ ኢትዮጵያን በብርሃኑ ሊያደምቃት፣ ኃይል ሆኖ ሊያበረታት ከጫፍ ደርሷል። በፈጣሪ ርዳታና በኢትዮጵያዊ ወኔ ሙሉ በሙሉ ግንባታውን አጠናቅቀን የልባችን እንደሚሞላ አልጠራጠርምና እንኳን ደስ ያለን» ብለዋል፡፡

### ማረሚያ

በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ረቡዕ ነሃሴ 4 ቀን 2014 ዓ.ም «ፍረዱኝ» በሚል አምድ «ፍርድ ተዛብቶብኛል፤ ሰበር ቅስሜን ሰብሮኛል» በሚል ርዕስ ገጽ 7፤ ሦስተኛው አንቀፅ ላይ «የቦሌ ክፍለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት» የሚለው «የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቦሌ ምድብ 1ኛ የቤተሰብ ችሎት፤ መዝገብ ቁጥር 92999» በሚል ተስተካክሎ እንዲነበብ በትህትና እንጠይቃለን፡፡ ስለተፈጠረው ስህተት የዝግጅት ክፍሉ ይቅርታ ይጠይቃል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያን ከብልጽግና ጉዞዋ የሚያቆማት ኃይል ሳለመኖሩ ሌላ ታላቅ ማሳያ!

ኢትዮጵያና ልጆቿ ፈተናዎችን በማለፍ አሁንም ድል በድል መሆናቸውን ቀጥለዋል፤ አዳዲስ የብስራት ዜናዎች ሲሰሙ የቆዩ ሲሆን፤ ትናንት ደግሞ ሌላ አዲስ ብስራት አዳምጠዋል:: በየካቲት 2014 በዩኒት አስር ብርሃን መስጠት የጀመረው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ እነሆ ትናንት በወርሃ ነሐሴ ደግሞ ዩኒት ዘጠኝ ሀይል ማመንጨት ጀምሯል:: በእዚህ ግድብ ግንባታ አሻራችሁን ያኖራችሁና እያኖራችሁ ያላችሁ መላ ኢትዮጵያውያን በሙሉ እንኳን ደስ አላችሁ!

ኢትዮጵያውያን በቁጭት ሲያነሱት በኖሩት ዓባይ ላይ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን በመገንባት ጨለማ ውስጥ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ብርሃን ከመስጠት አልፎም ተርፎ ለተለያዩ የልማት ተግባሮች በማዋል ይህን ታላቅ ወንዝ ራት ለማድረግ ተይዞ የነበረው ራእይ እውን ማድረጉ ቀጥሏልና ኢትዮጵያውያንንና መንግስታቸውን ደግሞ ደጋግሞ እንኳን ደስ አላችሁ ቢባል አይበዛምና አሁንም እንኳን ደስ አላችሁ!

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፣ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴና ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት በተገኙበት ትናንት ሁለተኛው ተርባይን የኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጨት በጀመረበት ሥነሥርዓት ላይ እንደተገለጸው፤ በ2014 በጀት ዓመት በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ተይዘው ከነበሩ ዋና ዋና እቅዶች መካከል የግድቡን ሁለት ተርባይኖች ሀይል ማመንጨት ማስጀመር አንዱ ነበር፤ ይህ እቅድ ሁለተኛውን ዩኒት ሀይል ማመንጨት በማስጀመር በስኬት ተጠናቋል:: ሌሎች በርካታ የግድቡ ስራዎችም እንዲሁ በስኬት ብቻ ሳይሆን አስቀድመውም ተከናውነዋል:: ይህም ሀገሪቱ በተለያዩ ዘርፎች የያዘቻቸው እቅዶች እየተሳኩ ለመሆናቸው ሌላ ታላቅ ማሳያ ነው::

ኢትዮጵያ፤ ለተፋሰሱ ሀገሮች በተለይም ለታችኛው የተፋሰሱ ሀገሮች ሱዳንና ግብጽ በተደጋጋሚ እንዳስገነዘበችው ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የምትገነባው በማገዶ እና በላምባ ጭስ እየተሰቃዩ ያሉ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎቿ ብርሃን እንዲያዩ ለማድረግ እንዲሁም ልማቷ እየጠየቀ ያለውን ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት ነው:: በግድቡ የሚያዘው ውሃ ይህን የኤሌክትሪክ ሀይል አመንጭቶ ጉዞውን ወደነዚሁ ሀገሮች ያደርጋል:: ይህንንም ማድረግ ተጀምሯል:: የኢትዮጵያ ጠላቶች እንደሚሉት፤ እስከ አሁን ወደ ግብጽና የሱዳን የሚፈሰው ውሃ አልቆምም:: ይህም ጠላቶቻችን ከአስር ዓመት በላይ ለሚሆን ጊዜ ሲያስወሩት የኖሩትን ውሸት ያጋለጠም ነው::

እነ ግብጽ እንደሚሉት ኢትዮጵያ የትኛውንም ሀገር ለመጉዳት ሃሳቡ የላትም:: በትብብር ማልማት ብትፈልግም ሰሚ አላገኘችም:: ሀገሮቹን ቆማ መጠበቅ አልነበረባትምና ማንንም ሳትጎዳ በራሷ አልምታ ብርሃን ለዜጎቿ ማድረስ ጀምራለች::

ኢትዮጵያ ጥረቷና ርብርቧ መልማት ነው:: ኢንዱስትሪዎቿ፣ የኃይል ያለህ እያሉ በኃይል እጥረት ሳቢያ ከማምረት አቅማቸው ከ50 በመቶ በታች እያመረቱ፣ ጨለማ ውስጥ የሚኖሩ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ብርሃን እየናፈቁ፣ ብርሃን ያገኙትም እየተቆራረጠባቸው አንዳንዴም ፈረቃ ውስጥ እየገቡ በመኖር ላይ መሆናቸው የማይካድ እውነታ ነው። በቀጣይ በሀገሪቱ የኢንዱስትሪ ልማትም ሆነ ዘመናዊ ግብርና እቅድ የኤሌክትሪክ ኃይል ወሳኝ ግብአት መሆኑ እየታመነበት ምንም አለ አላለ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ጥያቄ ውስጥ አይገባም:: ስለሆነም ሃገሪቱና ሕዝቦቿ ከ5 ሺ 150 ሜጋ ዋት በላይ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት ከአንድ አስርት ዓመት በላይ የደከሙበት የግድብ ግንባታ ላይ የሚደረግ የትኛውም አይነት ጫናና አፍራሽ ተግባር ቦታ አይኖረውም::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የዩኒት ዘጠኝ ኃይል የማመንጨት ሥራን ባስጀመሩበት ወቅት እንዳሉትም፤ ኢትዮጵያን ከጉዞዋ የሚያስቆማት የለም:: ለዚህም አባባል ማሳያዎቹ ታላቁ የህዳሴ ግድብ የደረሰበት ታላቅ ብርሃን የማመንጨት ምዕራፎች ናቸው::

ከግድቡ እንደሚያመነጭ ከሚጠበቀው የኃይል መጠን አኳያ አሁን ማመንጨት የተቻለው ጥቂቱን ነው:: በሀገራችን እንደ ቡና ያሉ ተክሎች ለመጀመሪያ ጊዜ ፍሬ ሲያሳዩ የምስራች አሳዩ ይባላል:: የግድባችን አንድ የምስራች በመጀመሪያው ተርባይን በመነጨው ኃይል አይተናል፤ ከግድቡ እንደሚመነጭ ከሚጠበቀው 5 ሺ 150 ሜጋ ዋት አኳያ ሲታይ በሁለተኛው ተርባይን የመነጨውም የምስራች ሊባል የሚችል ነው:: ከዓባይ ወንዝ በግድቡ ማግኘት የታሰበው እስከሚገኝ ድረስ ግንባታው ተጠናክሮ ይቀጥላል:: በተደጋጋሚ እንደተገለጸው ኢትዮጵያን ከዚህ ሊያቆማት የሚችል ምንም አይነት ምድራዊ ኃይል አይኖርም::

ኢትዮጵያን ከጉዞዋ የሚያቆማት ምንም አይነት ኃይል ስላለመኖሩ በርካታ አብነቶችን መጥቀስ ቢቻልም በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ እየተከናወነ ያለው ተግባር ዋናው ማሳያ ነው:: በእርግጥም ኢትዮጵያን ከጉዞዋ የሚያቆማት ኃይል አይኖርም!

ግድቡ ኃይል ለማመንጨት ምእራፍ ሲደርስ ብዙ ተደክሞበት ነው፤ ብዙ የጠላት ሴራዎች ተበጣጥሰው ነው:: አሁንም ይሄው ነው የሚሆነው:: ኢትዮጵያውያን ለግድቡ ያላችሁን የፋይናንስና ሌሎች ድጋፎች ማድረጋችሁን አጠናክራችሁ መቀጠል ይኖርባችኋል::

ኢትዮጵያ በፈተና ውስጥ እንደቆየች ሀገር አይደለችም:: ፈተናን እንደ ዕድል በመጠቀም ጣፋጭ ምርቶች የሚገኙባት፣ ውብ አዝመራዎች የሚታዩባት ሀገር ናት:: በቅርቡ የወጡ መረጃዎች የሚያመለክቱትም ይሄንኑ ነው::

በግብርናው ፤ በወጪ ንግዱ፣ በገቢ አሰባሰብ፣ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት፣ ወዘተ ከእቅድ በላይ እድገቶች ተመዝግበዋል:: በፕሮጀክት መጓተት የምትታወቀዋን ኢትዮጵያ ተስፋ የሚያመላክቱ በተያዘላቸው ጊዜና በጀት የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች የሚገኙባትም መሆን እየቻለች ነው::

ትናንት ደግሞ ሌላ ታላቅ የምስራች ሰምተናል:: ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት ጀምሯል:: ይህ ደግሞ ለመላ ኢትጵያውያን ታላቅ የምስራች ሲሆን፤ ኢትዮጵያ የብልጽግና ጉዞ ስኬት ሌላኛው ማሳያም ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


## ‹‹ኢትዮጵያውያን በሙሉ ባለ እድልም ፤ ባለ ድልም በመሆናችን እንኳን ደስ አላችሁ! እንኳን ደስ አለን !››

*- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ*

ክብርት ፕሬዚዳንት ፣ ክቡር ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፣ የተከበራችሁ ሚኒስትሮች ፣ ከሁሉ በላይ በዚህ ታላቅ ፕሮጀክት ላይ የተሳተፋችሁ ሰራተኞች እና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዛሬው ዕለት በምናስጀምረው ሁለተኛው ዩኒት እና አጠቃላይ ግድቡ የስራ ውጤት እንኳን ለእድልም ፤ እንኳን ለድልም አበቃን አበቃችሁ!፡፡

በታሪክ ውስጥ ማለፍ እና ታሪክ መስራት ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው ። በታሪክ ውስጥ ማለፍ እድል ነው። በታሪክ ውስጥ ማለፍ አንድ ሁነት ሲከወን ነበርኩ፤ አይቻለሁ፤ ሰምቻለሁ ፤ ብሎ መመስከር መቻል ነው። በዚህ ታሪክ ውስጥ ማለፍ ብቻ ሳይሆን ታሪክ መስራት ግን እድል ብቻ ሳይሆን ድልም ነው። በመገኘት እውቀትን ፣ ገንዘብን ፣ ሃሳብን ጉልበትን በመስጠት አንድ ሁነት እንዲከወን ማድረግ ከእድል ያለፈ ድል ስለሆነ እኛ የዛሬ የኢትዮጵያ ትውልዶች አሁን በሕይወት ያለን የኢትዮጵያ ዜጎች በሙሉ የዚህ እድልም ፤ የዚህ ድልም ተቋዳሽ ስለሆንን እንኳን ደስ ያለን እንኳን ደስ ያላችሁ ማለት እፈልጋለሁ፡፡

ይህንን ትውልድ ባለ እድል እና ባለድል የሚያደርገው ለአንድ ሺህ ዓመታት ሲታሰብ፤ ሲተለም ብዙዎች ሲመኙት የነበረውን ይህንን ግድብ፤ ይህንን ውሃ የመገደብ እና መጠቀም መሻት በአይኑ ያየ በእጁ የዳሰሰ እንዲሁም በእግሩ መርገጥ የቻለ ባለእድል ትውልድ ስለሚያደርገው ነው ። አባቶቻችን ተመኝተዋል ፤ አስበዋል ፤ አቅደዋል፡፡ እኛ ዛሬ ያየነውን ግን ማየት አልቻሉም፡፡ እኛ የቆምንበትም መቆም አልቻሉም፡፡ ሁሉ ቀርቶ የዛሬ ሶስት ዓመት ገደማ በዚህ ስፍራ አስረኛውን እና ዘጠነኛውን ዩኒት ጎን ለጎን ማየት የቻሉ ብዙ ሰዎች አልነበሩም፡፡ እና ዛሬ እዚህ የተገኛችሁ ሰዎችም በሚዲያ የሚከታተሉ ሌሎች ሰዎችም ኢትዮጵያውያን በሙሉ ባለ እድልም ፤ ባለ ድልም መሆናቸውን እንዲያስቡ እና በዚህም እርካታ እንዲሰማቸው መፈለጌን በዚህ አጋጣሚ መግለጥ እፈልጋለሁ፡፡

ሁላችሁም እንደምታውቁት ኢትዮጵያውያን ገንዘባቸውን፣ እውቀታቸውን ከዚያም አልፎ ሕይወታቸውን የገበሩለት ፕሮጀክት ነው፡፡ ብዙ ንጹሃን ዜጎች ከጥፋታቸው ውጭ ይህ ጉዳይ ተከውኖ በዚህ መንገድ እንድናየው ሕይወታቸውን ገብረዋል። ከዚህም ባሻገር በየመንገዱ የእለት ስራቸውን ሲሰሩ የነበሩ ሰዎች ስራው በዚህ ደረጃ እንዳይከናወን ከፍተኛ ተግዳሮቶች ገጥመውን ያውቃሉ ፤ መስዋዕትነት ተከፍሎ ያውቃል። የጸጥታ ተቋማት ብዙ ዋጋ ከፍለዋል። ይህ ሁሉ ሆኖ ዛሬ በእድል እና በድል እዚህ ስፍራ መቆማችንን አቅልለን ሳንመለከት ለላቀው ድል ደግሞ እንድንነሳ ማሳሰብ እወዳለሁ።

አባቶቻችን ይህንን ግድብ አስበዋል ፤ አልመዋል፤ ዘፍነዋል፤ ገጥመዋል ፤ ብዙ ቁጭት አስደምጠዋል። ነገር ግን እኛ ያ የታሰበውን ግድብ ከሃሳብ ወደ ተግባር ፤ ከመገድብ እና በበርካታ ፈተናዎች ውስጥ ከማለፍ አልፎ ዛሬ ሁለተኛውን ዩኒት ኢነርጂ ጀኔሬት ማድረግ ወደ ምንችልበት ማድረስ በመቻላችን ከተረት፣ ከዘፈን፣ ከቁጭት ፣ ከሃሳብ ፣ ከምኞት፣ ከራዕይ ተሻግሮ ሃሳቡን በተግባር ማየት እና መዳሰስ በመቻላችን ፤ ተረት የነበረውን ታሪክ ማድረግ በመቻላችን ፤ አይቻልም የተባለውን ተችሎ በማየታችን እንደዜጎች የምንኮራ ስንሆን ከዚህም በላይ ግን የአባቶቻችንን ትልም እና ፍላጎት በማሳካት ሀገራችንን በጸና መሰረት ላይ የማቆም የዚህ ትውልድ ዋነኛ ሃላፊነት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ብዙ ሰዎች ለልጆቻቸው ቤት ማውረስ ይፈልጋሉ፤ ሀብት ማውረስ ይፈልጋሉ ፤ ንብረት ማውረስ ይፈልጋሉ ፤ ነገር ግን ቤት ሳይኖር ሳሎን ማውረስ አይቻልም፡፡ መጀመሪያ ስለሳሎን ለማውራት ቤት ያስፈልጋል ፡፡ ቤት ለማውረስ ደግሞ ሀገር ያስፈልጋል፡፡ ሀገር የሌለው ሰው ቤት ማውረስ አይችልም ።

እኛ ኢትዮጵያውያን የጸናች፤ የበለጸገች ሀገር ማቆየት ከቻልን በዚያ ውስጥ ያለ ሀብት ፣ ቤት ፣ ንብረት ልጆቻችን በቀላሉ ሊወርሱ እንደሚችሉ ማሰብ ያስፈልጋል። በእኛ አጥር ውስጥ ፤ በእኛ ቤት ውስጥ ፤ በእኛ ሳሎን ውስጥ የአማረ ነገር ኖሮ በሀገራችን የተመቸ ነገር ከሌለ ሙሉ ስለማይሆን ሀገርን ማጽናት ማስቀጠል፤ ሀገርን ለማበልጽግ እና ለማስቀጠል በሚደረግ ጥረት ውስጥ አቅም በፈቀደ መጠን ተሳታፊ መሆን ከሁሉም ዜጎች የሚጠበቅ ይሆናል።

ይህ በእንዲህ እያለ የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት በተለይም ሱዳን እና ግብጽ በተደጋጋሚ እኛ ሃይል በማመንጨት ኢኮኖሚያችንን የማሻሻል ፤ በጨለማ ውስጥ የሚኖሩ ዜጎቻችን ብርሃን እንዲያገኙ ከመፈለግ ውጭ እነሱን የመግፋት ፤ የመጉዳት ዓላማ እንደሌለን በተደጋጋሚ ገልጸናል።

ዘንድሮ ሶስተኛው ሙሊት ያረጋገጠው 22 ቢሊዮን ሜትር ኪውቢክ ገደማ ውሃ መያዝ የሚያስችል ስራ ፤ እንዲሁም ሁለት ዩኒት ጄኔሬት ማድረግ የሚያስችል ስራ ቢሰራም በታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ላይ ምንም አይነት የውሃ እጥረት እንዳያጋጥም ፤ ኢነርጂ ጄኔሬት እያደርግን ከዚያ ባሻገር ቦተም አውትሌት የሚባለው ከውጭ የሚታየው በከፍተኛ ግፊት የሚሄደው ውሃ አንድም ቀን ሳይቋረጥ እንዲሄድ የተደረገበት ዋነኛው ዓላማ ሌሎች ወንድሞቻችን መጉዳት ሳይሆን እኛ የመጠቀም ፤ የማደግ ፍላጎት ስላለን ያንን በተግባር ለማሳየት ነው።

ይህ እየፈሰሰ ያለው ውሃ ቢገደብ በአጠረ ጊዜ ውስጥ ግድቡ ውሃ ሊይዝ ይችላል፡፡ ለእነሱ የሚገባቸውን እየለቀቅን እኛ በረጅም ጊዜ ውስጥ ውሃ የምንይዘው እነሱም ሳይጎዱ እኛም ሳንጎዳ በጋራ ለመበልጸግ ፤ ለማደግ ካለን ፍላጎት መሆኑን ተገንዝበው የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት በንግግር፣ በድርድር ፣ በስምምነት ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ከልብ አምነው ለዚያ እንዲተጉ፤ ከዚያ ውጪ ያለው ማንኛውም አማራጭ የጀመርነውን ነገር የማያስቆም እንዲሁ በከንቱ የሚያደክም መሆኑን ተገንዝበው ወደ ሰላም ፤ ወደ ድርድር ፤ በጋራ ለማደግ እንዲመጡ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪዬን ማቅረብ እፈልጋለሁ ፡፡

በዚህ ስራ ውስጥ በገንዘባቸው፣ በእውቀታቸው፣ እንዲሁም በሚዲያ ባላቸው የቋንቋ ብቃት ከዚያም ባሻገር እዚህ ቦታው ላይ በመገኘት ይህንን ስራ በታቀደለት እቅድ መሰረት እንዲከወን ጥረት ያደረጉ ሰራተኞች ፤ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ደስ ያላችሁ ! እንዲሁም እጅግ አድርገን እናመሰግናለን ፡፡ በእናንተ ጥረት ፤ በእናንተ ልፋት፣ በእናንተ እውቀት፣ በእናንተ ድካም ሀገራዊ ትልሞቻችን ተሳክተው ለዛሬ ስለበቃን እናመሰግናለን ! እንኳን ደስ ያላችሁ ማለት እፈለጋለሁ፡፡

በመጨረሻም የህዳሴ ግድብ አሁን ያለበት ደረጃ የሚያሳየው የኢትዮጵያ ብልጽግና እውን የሚሆን ፤ የኢትዮጵያን ብልጽግና ማንም ሊያቆመው እንደማይችል ፤ ይህ የኢትዮጵያ ሲዝን በመከወን በኢክሰለንስ በመጨረስ ወደ ሚቀጥለው ሌየር የሚያድግ መሆኑን ማሳያ ነው።

በዚህ ሰዓት ሁላችሁም እንደምታውቁት ውሃ የሚፈስብትን የመጨረሻውን ወለል ስድስት መቶ ለማድረስ እንዲሁም ግራ እና ቀኝ ያለውን ስድስት መቶ አስራ አንድ ለማድረስ ታቅዶ ሲሰራ የነበረ ቢያንስ ከአስር ቀን በፊት ተጠናቋል። ባለፈው ዓመት የነበረነው ችግር እየሰራን ውሃው የቀደመን ሲሆን ዘንድሮ ግን በነበረው እርብርብ ውሃውን ቀድመን ከአስር ቀናት በላይ ቀድመን የዓመት እቅዳችን ማሳካት የቻልነው በብዙ የኢትዮጵያ ወንድ እና ሴት ልጆች ጥረት በመሆኑ ያሰብነውን ማሳካት ብቻ ሳይሆን ቀድመን ማሳካት በመቻላችን ፣በግሪን ሌጋሲም ፣ በስንዴውም ፣ በኤክስፖርቱም በጀመርነው ስራ ሁሉ የምናየው የኢትዮጵያ ብልጽግና የማይቋረጥ ብቻ ሳይሆን ሁላችንም የምናየው መሆኑን የሚያረጋግጥ መሆኑን የተገነዘብንበት፣ የተማርንበት ስለሆነ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ ብልጽግና ለሚደረገው ጉዞ የእራሱን አሻራ እንዲያስቀምጥ ፤ ከአቧራ እራሱን እንዲጠብቅ አደራ እያልኩ ይህ ሁሉ እንዲከወን ፤ እንዲጨረስ ለረዳን የኢትዮጵያ አምላክ ፣ የኢትዮጵያ ፈጣሪ፣ እጅግ ከፍተኛ ምስጋና እያቀረብኩ ለሚቀጥለው ጊዜም ፈጣሪ ኢትዮጵያ እና ሕዝቦቿን እንዲባርክ ኢትዮጵያ ህልሟን እንዲያሳካ ፣ የኢትዮጵያን የእጅ ስራ እንዲከናውን የሁላችን ጸሎት እና ልመና እንዲሁም ምስጋና እንዲሆን እያሳሰብኩ እንኳን ደስ ያለን ፤ እንኳን ደስ ያላችሁ!

በህዳሴ የተጀመረው ድል በሁሉም ይቀጥላል፤ የኢትዮጵያን ብልጽግና በጋራ እናያለን ! ብልጽግና ከተግዳሮት ውጭ አይደለም ተግዳሮቶች ይበልጥ እንድንማር ፣ እንድንበረታ፣ እንድንጠነክር የሚያደርጉ መሆናቸውን ተገንዝበን እጅ ለእጅ ተያይዘን ለትልቁ ድል እና ብልጽግና እንድንቆም አደራ ማለት እፈልጋለሁ፡፡ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ ፤ እንኳን ደስ ያላችሁ ! እንኳን ደስ ያለን !

# አባይ...የጋራ ስማችን

**በትረ ሙሴ መልከ (ኢትዮጽ)**

የአማርኛው መዝገበ ቃላት አባይን ዋና አባት ሲል ይገልጸዋል። ከዚህ እውነት በመነሳት አባይ ማለት ዋና ማለት እንደሆነና አባት ማለት እንደሆነ እንደርስበታለን። ይህ ስም የስሞች ሁሉ በኩር፣ የክብሮች ሁሉ ቁንጮ ነው። ይህ ስም የእኛ ስም ነው። ይህ ስም የኢትዮጵያውያንን ባህልና ታሪክ ተንተርሶ ነፍስ የዘራ ነው። ይህ ስም እትብቱን ከእትብታችን ቀላቅሎ፣ ጥቁርነትን ለብሶ፣ ታሪክና ስልጣኔአችንን ተጋርቶ ከጉያችን መንጭቶ የሚፈስ ነው።

ታዲያ አባት ቢባል ምን ያንስበታል? አባይ ዋናችን ነው..ከዚህ ውጪ ምንም ሊሆን አይችልም። ለዘመናት በአቅምና በኢኮኖሚ ችግር አባትነቱን ግብጾች ቀምተውን በራሳችን ታሪክ ባይተዋር አድርገውን ነበር። ለዘመናት በእኛ አባትነት ግብጽን ጨምሮ የታችኞቹ ተፋሰስ ሀገራት ሲያጌጡና ከፍ ሲሉ ነበር። ዘመን ተቀይሮ ይሄኛው ትውልድ በአቅምም በኢኮኖሚም በርትቶ አባይን እየገደበው ይገኛል፤ ምን መገደብ ብቻ ሀይል ማመንጨትም ጀምሯል።

በርግጥ ለኛ ኢትዮጵውያን አባይ የጋራ ስማችን ነው...መታወቂያችን። ኢትዮጵያዊነት የወል ስም ካለው አባይ ነው። በብዙ ነገር ተለያይተን በአባይ ጉዳይ ላይ ግን አንድ ነን። ምክንያቱም አባይ በጋራ የጻፍነው የጋራ ታሪካችን ስለሆነ። በኢትዮጵያ ምድር እንደ አባይ በጋራ ጀምረን በጋራ ልንጨርሳቸው የሚገቡ በርካታ ነገሮች አሉ። መለያየት ያበላሻቸው፣ እኔነት ያጸለማቸው በጣም ብዙ ጉዳዮች አሉን። እኚህ ጉዳዮቻችን ተጀምረው እንዲያልቁ፣ ስኬትና ከፍታ፣ እድገትና ስኬት እንዲሆኑን በአንድነት መቆም አለብን።

አባይ የአንድነታችን ውጤት ነው። አለም በተነሳብን ጊዜ፣ ሀያላኖቹ ለግብጽና ሱዳን ወግነው በተነሱብን ጊዜ አንድ ላይ ነበርን። በብዙ ልዩነት ውስጥ አብረን ነበርን። ይሄን ነው የኢትዮጵያዊነት ቀለም የምላችሁ። ይሄን ነው የጋራ ስማችን የምላችሁ። ይሄ አንድነት ዛሬ ላሉብን ችግሮች አስፈላጊ ነው። አባይን በጋራ እንደገነባነው ሁሉ በጋራ የምንወጣቸው በርካታ ሀገራዊ እንከኖች አሉብን። አንድነት ምን ያህል ሀይል እንደሆነ አባይ ምስክራችን ነው። የአባይ ግድብ፣ የአባይ ምስጢሩ የአንድነታችን ውጤት ነው።

በአባይ ጉዳይ ግብጾች ተኝተው አያውቁም። ዛሬም የውሸትና የፖለቲካ ሸሮችን እየጎነጎኑ ተስፋችንን ሊነጥቁን እያሴሩብን ነው። ትውልዱ ግን በአባቱ የማለ፣ በአባቱ ቀልድ የማያውቅ ሆኖ በግብጽና ሱዳንም ጩኸት ውስጥ ታሪክ እየሰራ ይገኛል። ይሄ ትውልድ ከእንግዲህ ወደ ኋላ የማይል ነው። ዋናውንና አባቱን ለባዕድ ሰጥቶ በድህነትና በኋላ ቀርነት መኖር አይፈልግም። አይደለም በአባይ ጉዳይ ወደኋላ ሊል ቀርቶ እነዛ በአቅም ማነስ በግብጾች የበላይነት ያለፉት የአባቶቹ ዘመናት እንኳን የሚያስቆጩት ናቸው።

ግብጾች የነጠቁንን አባታችንን ማስመለስ የዚህ ትውልድ የቤት ስራው ነው። ለዘመናት በአባታችን በአባይ ግብጽ ስታጌጥ ኖራለች። ከእንግዲህ አባይ የእኛ ነው። ካባ ለብሶ፣ ዘውድ ጭኖ ትንሳኤውን ሊያሳየን እነሆ ከአፋፍ ደርሷል። ኢትዮጵያውያን በአንድ ያዜምንለት፣ በአንድ የዘፈንለት አባይ ሊምሸር ዋዜማ ላይ ነው። ጨለማዎቻችን ሊነጉ፣ ተስፋዎቻችን ብርሀን ሊያዩ...ኢትዮጵያ ልትስቅ እንሆ ትንሽ ብቻ ይቀራል።

አባይ የገነት መቀነት ነው። ወገቧን ሸብ ያደረገችበት። ገነት ያጌጠችው አባይን ተደግፋ፣ አባይን ጠምጥማ ነው። አባይ የኤዶም ገነት ክንብንብ ነው...አንገቷ ላይ ጣል ያደረገችው። አባይ እምነታችን፣ ጽናታችን፣ የአንድነታችን ክር ነው። አባይ ተስፋችን፣ ትንሳኤአችን፣ የከፍታችን ማማ ነው። በአባይ ግድብ ተስፋን የሰነቁ፣ ነገን አሻቅበው የሚያዩ ነፍሶች በኢትዮጵያ ምድር አሉ። እኚህ ነፍሶች እኔና እናንተ ነን። እኚህ ነፍሶች መጪው ትውልዶች ናቸው። ከምንበላው ላይ ቀንሰን፣ ከሌለን ላይ ገምሰን ነው ከዘመናት ኩብለላው የመለስነው። አባይ በተፈጥሮ ውልደት ከከበቡንና ታሪክና ባህላችንን ከወረሱ እሴቶቻችን አንዱና ዋነኛው ነው።

በዚህ ርስታችን ማጌጥ አለብን። ከዚህ ህብስታችን መብላት አለብን። ኢትዮጵያውያን ክፉዎች አይደለንም። እውነትን ሸተው ለተጠጉን ካለን ላይ ማካፈል የለመድን ህዝቦች ነን። እኛ አብረን እንብላ ስንል ግብጽና ሱዳን ለብቻችን ካልበላን እያሉ ነው። ይሄ ትውልድ ርስቱን አሳልፎ መስጠት አይፈልግም። ከበሉ አብረውን ይብሉ ካልበሉ ግን በርስታችን ላይ የመጠቀም ሙሉ መብት አለን፤ አባይን ገድበን የመጠቀምና የመልማት መብት።

ሱዳንና ግብጽ የከፉብንን ያህል እኛ ለነሱ ከፍተን አናውቅም። ከትናንት እስከዛሬ አብረን እንልማ፣ አብረን እንደግ እንዳልን ነው። ነገር ግን ወልደው ባሳደጉት የክፋት ሃሳቦቻቸው ከጀመርነው የእድገት ጎዳና ሊያደናቅፉን ብዙ ለፍተዋል አሁንም እየለፉ ነው። በተለይ አባይን ለመገደብ በተነሳንበት ሰሞን ከግብጽና ከወዳጆቿ እንዲሁም ከአለም አቀፉ ማህበረሰብ የደረሰብን ጫና ቀላል የሚባል አልነበረም።

አሁንም አልተኙም...የተሳሳተ መረጃዎችን በማሰራጨት፣ በአባይ ጉዳይ ያለንን አንድነት ለማላላት በርካታ ሴራዎችን በመጎንጎን ላይ ናቸው። እኛ ግን አሁንም በአባይ ጉዳይ ላይ አልቆምንም፤ አልተለያየንም፣ አንድ ላይ ነን። በተለይ የመጀመሪያውን የውሃ ሙሌት በጀመርን ሰሞን፣ በተለይ ሁለተኛውን የውሃ ሙሌት ጀምረን ሀይል ማመንጨት ስንጀምር የሆኑት መሆን እንዲህ በቀላሉ የሚገለጽ አልነበረም። አሁንም የተሳሳተ መረጃዎችን በማሰራጨት ከምዕራባውያን ወዳጆቻቸው ጋር እያሴሩብን ነው።

እኛ ግን ያው እንደ ትናንቱ ነን። የግብጽን የሀሰት ወሬ ችላ ብለን ስለ አባይ ጎንበስ ቀና እያልን ነው። እኛና ግብጽ አይሁድንና ክርስቶስን ነን። በዛ በጎለጎታ፤ በርባን ተፈቶ ክርስቶስ ሲሰቀል ብዙዎች ደስ ብሏቸው ነበር። አሁንም የግብጽ ወዳጆች ኢትዮጵያ ከስራ ግብጽ እንድታተርፍ የሚፈልጉ ናቸው። ይሄ ግን አይሆንም፤ ምክንያቱም ትውልዱ ትንታግ ትውልድ ነው። በዚያ ጊዜ ከአይሁድ ጫጫታ ይልቅ ጲላጦስን ያስፈራው የክርስቶስ ዝምታ ነበር። እኛም የግብጾች ጩኸት ምናችንም ነው። እንደ ክርስቶስ ዝም ብለን የተደቀኑብንን መሰናክሎች ተረማምደን ትንሳኤአችንን እናያለን።

አባይ አባታችን ነው፤ እናቱ ደግሞ ኢትዮጵያ ናት። ከአብራኳ ወጥቶ፣ በአብራኳ አድጎ የበለጸገ ልጇ። ታዲያ አባዬ ብለን ብንጠራው ማን ምን ያገባዋል? ዛሬም ነገም መቼም አባይ የእኛ ነው። ለሚወዱን በፍቅር ለተጠጉን እናጋራዋለን። አባይን ከመገደብና በአባይ ላይ ከመጠቀም የሚያግደን ምንም ምድራዊ ሀይል የለም።

አንዳንድ ውሸቶች ሲቆዩ ወደ እውነት ይቀየራሉ። በተለይ ውሸት ፈጣሪ ግለሰቦችና ፖለቲከኞች ሲኖሩ እውነት ክብር ያጣል። የአባይ ጉዳይ በግብጽ ላይ እንደዚህ ነው። ለዘመናት ያለማንም ከልካይ ተጠቀሙበት፤ ከዛም የእኛ ብቻ ነው፣ የሚመነጨውም ከግብጽ ምድር ነው ሲሉ ማመን ጀመሩ። ማመን ብቻ አይደለም ያላመኑትን ማሳመን ጀመሩ። ትውልዱ እውነትን ሽሮ አባይ የግብጻውያን እንደሆነ አምኖ እንዲቀበል ብዙ ለፉ። ለልጆቻቸውም ስለ አባይ ውሸት ነገሩ።

በዚህ አላበቁም፤ በአባይ ጉዳይ ላይ የትምህርት ስርዐት ገንብተው ልጆቻቸውን ስለአባይ ውሸት ማስተማር ጀመሩ፤ አባይ የእኛ ነው ሲሉ። አሁን ለግብጻውያን አባይ ማለት ከግብጽ የሚመነጭ፣ ለግብጽ ህልውና የተሰጠ አምላካዊ ስጦታ ነው። ይሄ በዘመናት የውሸት አሉባልታ ውስጥ የተፈጠረ እውነት ነው።

አባይ የኢትዮጵያውያን ነው። ውልደቱ፣ እድገቱ ከሰከላ ማህጸን ነው። አሁን ትግላችን በግብጻውያን ልብ ውስጥ የታተመውን የውሸት እውነት ፍቆ አባይ የሀገራቱ ህዝቦች የጋራ ሀብት እንደሆነ ማሳየት ፤ አባይን በጋራ እንድንጠቀመው ማድረግ ነው።

በግብጽ ምድር ለአባይ የተዘፈነውን ያህል ለማንም አልተዘፈነም። ዛሬም ድረስ የጉዳያቸው አንደኛ ነው። ብሄራዊ ክብራቸው፣ ታሪካዊ ህልውናቸው አድርገውት ለዘመናት ኖረዋል። ይሄ የውሸት ትርክት በዚህ በእኔና በእናንተ ተሸሮ አባይ የጋራ ነው ስንል ተነስተናል። ትግላችንም ፍሬያማ ሆኖ ለጋራ ተጠቃሚነት እየገደብነው ብቻ ሳይሆን ብርሃኑንም እያየነው ነው። የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር የቀረን ትልቁ ነገር በአንድነት የገነባነውን፣ በአንድነት የደከምንለትን የህዳሴ ግድባችንን ማጠናቀቅ ነው። ይሄም ከሁለት አመት ብዙም የሚዘል አይሆንም። የሚቀረን በጋራ ትንሳኤአችንን ማጣጣም ነው። የሚቀረን እንደ ህዳሴ አይነት ሌሎች ግድቦችን መስራት ነው።

በነገራችን ላይ ግብጻውያን አባይን የህልውናቸው መሰረት ያደረጉበትን ብዙ ማስረጃዎችን ማየት እንችላለን። ግብጽ ውስጥ በአባይ የሚምሉ አሉ። ግብጽ በየአመቱ ከአምስት ሺ በላይ የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን ታስመርቃለች፤ በጣም የሚገርመው ደግሞ እነኚህ ሁሉ ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሁፋቸውን የሚሰሩት በአባይ ወንዝ ላይ መሆኑ ነው። ግብጽ ውስጥ አባይ ለብዙ ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሁፍ ሃሳብ ነው። ይሄ ማለት ግብጾች በአባይ ዙሪያ ምን ያህል ርቀት እንደተራመዱ የሚያሳይ ነው። አሁን ጊዜው የእኛና የአባይ ነው። በአባይ ላይ የግብጽ የበላይነት አክትሟል። አባይ ወደ እናቱ ተመልሷል።

በየትኛውም መስፈርት ቢታይ የኢትዮጵያ ታላቁ ህዳሴ ግድብ መስራት ግብጽና ሱዳንን አይጎዳም ይጠቅማቸዋል እንጂ፤ ግን ውስጣቸው ያስቀመጡት የኔነትና የብቻ ሃሳብ ስላለ አባይን መጋራት አይፈልጉም።

ይሄ ሃሳብ ምን ያህል እውነት እንደሆነ ለማየት ጥቂት ምሳሌዎችን ላስቀምጥ። ካቻምና የመጀመሪያ የውሃ ሙሌት ስናከናውን ካጠቃላዩ የውሃ ይዘት 4 በመቶ ብቻ ነበር የተጠቀምነው። ቀጥለን በአመቱ አምና ማለት ነው 13 በመቶ ብቻ ነው ለሙሌት የተጠቀምነው፤ ይሄ ማለት በመጀመሪያው ሙሌት 96 በመቶው በሁለተኛው ሙሌት ደግሞ 87 በመቶው ውሃ ወደ ግብጽና ሱዳን ፈሷል ማለት ነው። ከዚህ እውነት በመነሳት የውሃ እጥረት ይፈጠራል፣ የተፋሰሱ ሀገራት ይራባሉ የሚሉት የግብጽና የሱዳን አሉባልታዎች ውሸት መሆናቸውን እንደርስበታለን።

የግብጽና ሱዳን ስጋት የኢትዮጵያን ብልጽግና ከመፍራት የመነጨ ነው። ኢትዮጵያን ከመፍራት፣ ብልጽግናዋን ከመስጋት የመነጨ ስሜት ነው። ኢትዮጵያ ሀገራችን ከህዳሴ ግድባችንና ከዚህ በኋላም በምትገነባቸው ግድቦች የምታገኘው የሀይል፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የስልጣኔ፣ የዘመናዊነት ጸጋ ስጋት ሆኗቸው ነው ዛሬ ላይ ይሄን ሁሉ ችግር እየፈጠሩ ያሉት።

የህዳሴ ግድባችን ከሃሳባችን ያልወጣ፣ ከሃሳባችን የማይወጣ የህልውናችን ማህተም ነው። ጠላት ያው ጠላት ነው፤ ጥሩ ነገር አያወራም። ገና ከዚህ በኋላም የተለያዩ የውሸት ወሬዎችን እንሰማለን። ከእኛ የሚጠበቀው እንደ ክርስቶስ ዝም ብለን እየሰራን ወደ ትንሳኤአችን መጓዝ ነው።

አባይ አባታችን ነው፤ ከግንባታው የሚያስቆመን ማንም የለም። የግብጾች ህልውና እንደመሆኑ ለእኛም ህልውናችን ነው። በአባይ ግድብ ላይ መቶ ሃያ ሚሊዮን ድሀ ህዝቦች ተስፋን ሰንቀዋል። እምነትን ጥለዋል። በአባይ ግድብ ላይ መጪው ትውልድ ኩራትና ብኩርናን በዛሬዎቹ እኛ ላይ ጥሏል። ታዲያ አባይ እህል ውሃችን ቢሆን ምን ይገርማል?

> **በአባይ ጉዳይ ግብጾች ተኝተው አያውቁም። ዛሬም የውሸትና የፖለቲካ ሸሮችን እየጎነጎኑ ተስፋችንን ሲነጥቁን እያሴሩብን ነው። ትውልዱ ግን በአባቱ የማለ፣ በአባቱ ቀልድ የማያውቅ ሆኖ በግብጽና ሱዳንም ጩኸት ውስጥ ታሪክ እየሰራ ይገኛል። ይሄ ትውልድ ከእንግዲህ ወደ ኋላ የማይል ነው**

# ሀገራዊ እሴቶችን ለማፍካት

**አስናቀ ፀጋዬ**

ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ፣ የሶስት ሺ ዓመት ታሪክ ያላት፣ የበርካታ እምነት፣ ቋንቋ፣ ባህል፣ ጥበብና ፍልስፍና መኖሪያ ናት እየተባለ ሲነገር በተደጋጋሚ ይደመጣል ሕዝቧም ሰው አክባሪ፣ በጉርብትና ተዋዶ የሚኖር እንደሆነ ይነገርለታል ጠላትን በጋራ ተባብሮ መዋጋትም የጥንት ባህሉ ነው መረዳዳት፣ መተባበርና ፈጣሪን መፍራትም ሁነኛ መገለጫው እንደሆነ ይጠቀሳል

እነዚህ መልካም የሆኑ የኢትዮጵያ እሴቶች ከትውልድ ትውልድ በቅብብሎሽ በረጅም የታሪክ ኡድት ውስጥ ተጉዘው የዛሬው ትውልድ ላይ ደርሰዋል ሆኖም እነዚህ እሴቶች ልክ እንደበፊቱ በዛሬው ትውልድ ይበልጥ ጎልተው መውጣት አልቻሉም እያደጉና እየጎለበቱ ከመሄድ ይልቅ እየደበዘዙና እየኮሰሱ መጥተዋል

ወጣት ሽማግሌ መስማት ትቷል እርስበርስ መከባበርም ጠፍቷል አንዱ በአንዱ ላይ ጨክኗል እርስበርስ መገዳደልም እየተለመደ መጥቷል ፈጣሪን መፍራት እየተረሳ የመጣ ይመስላል ለመሆኑ እነዚህ መልካም ሀገራዊ እሴቶች በጊዜ ሂደት እንዴት እየተሸረሸሩ ሊመጡ ቻሉ? የተሸረሸሩ እሴቶችንስ እንዴት ወደነበሩበት መመለስ ይቻላል? በሚሉና መሰል ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ‹‹የጋራ እሴቶቻችን ስለ ኢትዮጵያ›› በሚል መሪ ሃሳብ የፓናል ውይይት አካሂዷል ሁለት ጽሁፎች ቀርበዋል

በዚህ የፓናል ወይይት ለውይይት መነሻ የሚሆን ጽሁፍ ያቀረቡት የሃይማኖት አስተምህሮ ሊህቅ ኡስታዝ አቡበክር አህመድ እንደሚናገሩት ሀገር ሲታሰብ እንደማሕረሰብ እድገትን፣ የተሻለ ነገርን፣ በመልካም መሸጋገርንና ተስፋን ሰንቆ መጓዝ ያስፈልጋል ችግሮች ሲከሰቱም በመነጋገር፣ የጋራ እሴቶችን በማጎልበት፣ የጠፉትን በመፈለግ፣ እንደ አዲስ ወደፊት ለመራመድ እጅ ለእጅ በመያያዝና በመነጋገር ብሎም አብሮ በመሆን ነው ሀገሪቷን ወደተሻለ ደረጃ ማሸጋገር የሚቻለው ይህም የሁሉም ዜጋ ድርሻና ሃላፊነት ነው

ኡስታዝ አቡበከር እንዳብራሩትም የጋራ እሴቶችን ምሁራን ሀገራዊ፣ የማሕረሰብና የግለሰብ እሴቶች እያሉ በብዙ መንገድ ያቀርቧቸዋል አሁን ካለው ሀገራዊ ሁኔታ አንፃር ሀገራዊና ማሕረሰባዊ የሥነ-ምግባር እሴቶች ጋር ማተኮሩ መልካም ነው እየተሸረሸሩ ያሉት እሴቶችም በአብዛኛው እነዚህ ናቸው

እንደሀገር በሚደርሱ የተለያዩ ውጣውረዶች ሲታለፍ የኢትዮጵያዊነት ትልቁ መሰረት በታሪክ የረጅም ጊዜ ተሞክሮ ያላቸው ሕዝቦች መኖራቸው ነው ወደኋላ ለመመለስም እድል አለ ወደኋላ በመመለስ ፍተሻ ቢደረግ ቆም ብሎ ለማሰብና ወደተሻለ አቅጣጫ ለመሄድ የሚያስችሉ መሰረቶች አሉ እነዚህን መሰረቶች በማሰብም ነው ኢትዮጵያውያን ወደቀደመው ማነነታቸው ለመመለስ የሚቸገሩ ሕዝቦች አይደሉም የሚባለው

ኢትዮጵያውያን ትናንት የመጡ ወይም ትናንትና ላይ ቆመው መውጪያ መግቢያ የሚፈልጉ ሕዝቦችም አይደሉም ከዚህ አኳያ በብዙ መልኩ የኢትዮጵያውያን ታሪክ ማንነት አንድ የሚያደርግና በብዙ መልኩ እድል የሚሰጥ ነው

እንደ ኡስታዝ አቡበከር ገለፃ ዛሬ ላይ ትልቅና ሃያል ሀገር ተብሎው ከሚቆጠሩት እንደአሜሪካ ያሉ ሀገራት እንደትልቅ እሴት ከሚያነሷቸው ውስጥ ስድስቱ ግለሰባዊ ነፃነት፣ ራስን ችሎ መቆምና በራስ መመካት፣ የስኬት እድሎችን ሁሉ በእኩልነት እንዲያገኙ ማድረግ፣ የውድድር መንፈስ፣ ጥሩ ሕይወት መኖርና ጠንክሮ መስራት ናቸው አብዛኛዎቹ እሴቶች ከግለኝነት ጋር ይቆራኛሉ ለዛም ነው ትልቅ ሀገር፣ ትልቅ ሕዝብ፣ ዓለምን መምራት የቻለ ግን በኑሯቸውና በማንነታቸው ሲታዩ የኢትዮጵያውያንን ማንነትና እሴት ግዝፈት ይነሳል

አብሮነት፣ የጋራ የሆነ ማንነትና መከባበር እንደ ኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መገለጫዎችና ማሳያዎች ናቸው ተመሳሳይ ያጋራ መሰረቶችና ብዙ



ኡስታዝ አቡበክር አህመድ



ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ

**ወጣት ሽማግሌ መስማት ትቷል እርስበርስ መከባበርም ጠፍቷል አንዱ በአንዱ ላይ ጨክኗል እርስበርስ መገዳደልም እየተለመደ መጥቷል ፈጣሪን መፍራት እየተረሳ የመጣ ይመስላል ለመሆኑ እነዚህ መልካም ሀገራዊ እሴቶች በጊዜ ሂደት እንዴት እየተሸረሸሩ ሊመጡ ቻሉ?**

ኢትዮጵያውያኖችም የሚገለጹባቸው ሀብቶች ነበሩ እነዚህ እየጠፉ ሲመጡም ነው ሀገሪቱ አደጋ ላይ እየወደቀች የመጣችው ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሶስት ኢትዮጵያዊ እሴቶች ማለትም ሃይማኖተኛነት፣ መተባበር (መተጋገዝ) እና አብሮነት የተገነቡት በጋራ አብሮ ከመኖርና በታሪክ ውስጥ ካለፉ የአብሮነት ሂደቶች ናቸው

ከተለያዩ እምነቶች ተቀድተው የኢትዮጵያን አካል የሆኑ፤ ባህልና ልምድ የተደረጉ እንዲሁም በተለያዩ ውጣውረዶች ውስጥ በማለፍ አንዱ ከአንደኛው ጋር ፈተና ሆኖ ወድቆ ተነስቶ ከጥፋት በመማር የተገነቡ አብሮነቶች፤ እነዛና መሰል ሂደቶች የኢትዮጵያውያን ትልቅ እሴቶችና መገለጫዎች ናቸው ዛሬ ላይ ግን እነዚህ እሴቶች በመሸርሸራቸው ሀገር ፈተና ላይ ወድቃለች የምትታሰበው ኢትዮጵያም በብዙ መልኩ ለችግር ተጋልጣለች

የአባቶች በጎነት፣ ደግነትና መልካምነት የኢትዮጵያውያን የሚኮሩበት ማንነት ነው ይህን ፈለግ መከተል ካልተቻለ ግን የአሁኑ ትውልድ ማፈሩ አይቀርምሀገርም ለአደጋ መጋለጧ ሳይታለም የተፈታ ነው

የቀድሞ ኢትዮጵያዊ እሴቶችንና መገለጫዎችን ወደነበሩበት ለመመለስ ተረኛው ትውልድ ራሱን ማየትና መመልከት ይኖርበታል የጋራ የሆኑ የሥነ -ምግባር እሴቶች ተጠብቀው እንዲሄዱና የቀድሞ አባቶቻችንና እናቶቻችንን መስለው እንዲኖሩ ሊጠበቁ፤ ከተበላሹ ሊስተካከሉ፤ ከጠፉ ደግሞ ሊመለሱ ይገባል ለዚህም መፍትሄው የጋራ ነው

ኢትዮጵያ ስትታሰብ ነገን እንድናስብና ተስፋ እንድናሳድር ያደርገናል በተቃራኒው ክፋቱን፣ ፈተናውንና መከራውን የምናስብ ከሆነ ወድቀናል ከዚህ አንፃር በጋራ ወደፊት መንቀሳቀስ ያስፈልጋል በርገጥኝነትም የትናንት ማንነት እያለ ኢትዮጵያ አትጠፋም ወደከፍታው ለመመለስና የያኔዋ ኢትዮጵያ ተመልሳ እንድትመጣ ትልቅ ስራ ይፈልጋል ይቅርታ፣ መከባበር፣ አውቅና መሰጣጣት፣ አብሮነትን ማመንና በጋራ መቀበል ያስፈልጋል

ሌላኛው ጽሁፍ አቅራቢ የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ ናቸው ፕሮፌሰር መስፍን እንደሚሉት ኢትዮጵያ የበርካታ ሃይማኖቶችና ባህሎች መገናኛ ቦታ ነች የፍቅር ብቻ ሳይሆን የባህል መነሻ ነች እያንዳንዱ ዜማም የሚነሳው ከዚህች ሀገር ነው አምስቱም የዜማ አይነቶች የፈለቁት ከዚች ሀገር ነው ትልልቅ የሃይማኖት አባቶችና እናቶች ከዚች ሀገር ፈልቀዋል

ትግራይ የክርስትናና የእስልምና በር እንደሆነ ሁሉ ወሎም የእስልምናና የክርስትና መዳበሪያ ቦታ ነች የምትከበርና እንደተምሳሌት የምትወሰድ ከተማም ነች ታዲያ ይህ ሁሉ የሚነገርላት እነዚህ ሁሉ እሴቶች አሏት የምትባል ሀገር ምን ነካት? ምን ሆነች? ለምንድን ነው እዚህ ደረጃ ላይ የደረሰችው? የሚለውን መጠየቅ ያስፈልጋል

የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ዋናውና ትልቁ ስራው ሕዝቦች እንዲደማመጡ ማገዝ ነው አስካሁን ሕዝቦች ተነጋግረዋል ንግግራቸው ከአንደበትና የምልክት ንግግር አልፎ ወደመሳሪያ ንግግር ከተሸጋገረ አስርት ዓመታትን አስቆጥሯል ስለዚህ በመሳሪያ ንግግር የመጣው ውጤት ታይቷል መገዳደልን፤ መፈናቀልንና ስደትን ይዞ መጥቷል

ለዘመናት ጸንተው የቆዩ ኢትዮጵያዊ እሴቶች ተሸራርፈው ድምጥማጣቸው የጠፋበት ዘመን ላይ ተደርሷል ይህ ሲባል ትልልቅና ተምሳሌት የሚሆኑ ሰዎችን አላሳጣም ትልልቅ አባቶችንና እናቶችን አልከለከለም ግን እነዚህ እናትና አባቶች 120 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ አንድ ወለል ለማምጣት ምን ያህል አቅም ፈጥረዋል? የሚለው ወሳኝ ጉዳይ ነው ለዚህም ነው ወጣቶች ላይ ላለፉት ሰላሳ፣ አርባ፣ ሃምሳና ስልሳ ዓመታት ምን ያህል ሰርተናል? ብለን የምንጠይቀው

ዋና ኮሚሽነሩ እንደሚያብራሩት የኢትዮጵያ እሴቶች በየእንዳንዱ ዝርዝር ሲታዩና አብሮ መብላት፣ መስገድ፣ ማምለክና ጠላት ሲመጣ በጋራ ሆኖ መመከት የመሳሰሉትና ሌሎች እሴቶች የት ጋር ነው የታጠፉት? ብሎ መጠየቅ ግዴታ ነው እጥፋቱ የት ጋር ነው የሚለውን መርምሮ ለማግኘት ለባለሙያዎች ሃላፊነቱን መስጠቱ ተገቢ ነው እጥፋቱ የዛሬ ሰላሳና አርባ አመት ወይም ከዛም በፊት እየታጠፈ መጥቷል ማለት ይቻላል አንድ በጋራ የሚያስማማው ጉዳይ ግን እጥፋቱ በጣም ከፍተኛ መሆኑ ነው

ኢትዮጵያ የደጋጎች፣ የሃይማኖተኞች፣ የመቻቻል ሀገር ከሆነች እንዲህ አይነት የእርሰበርስ ግጭት ይከሰታል ተብሎ አይታሰብም ሆኖም በሚያሳዝን ሁኔታ ይህ ነገር ተከስቷል አንድ ሚሊዮን ሕዝብ አልቋል፤ በኢትዮጵያ ደረጃ የተከሰተው በሩዋንዳ ደረጃ ከተከሰተው በምን ይለያል የሚለውን ለታሪክ ምርምርና ለሚመለከተው አካል መተው ነው

ከዚህ አንፃር በዚች በተረፈች አነስተኛ ጊዜ ኢትዮጵያኖች መነጋገር አለባቸው በመሳሪያ ተነጋግረዋል፤ የትም አልደረሱም ስለዚህ ተቀራርበው መመካከር መቻል አለባቸው ምክክሩ ሲካሄድ ታዲያ ኢትዮጵውያን የእኩልነትን ንግግር ወደ ጠረጴዛ ማምጣት አለባቸው

ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የሚያደርገው ዋናው ስራው ሁሉም ኢትዮጵያውያን ያለምንም አድልዎና መገለል ስለኢትዮጵያዊነት ምንድን ነው የሚሉት? አጀንዳዎቻቸው ምንድን ናቸው? ምንን ማቅረብ ይፈልጋሉ? በምን አካባቢዎች ላይ መወያየት ይፈልጋሉ? በሚሉና እጅግ መሰረታዊ በሆኑ ችግሮች ላይ እንዲወያዩና መፍትሄ እንዲያመጡባቸው ነው

የምክክር ኮሚሽኑ ዋና ስራ ሀገራዊ እሴቶችን እንደመሳሪያ በመጠቀም ዋናውና ትልቁ ስራ ሕዝቡ ከላይ ወደታች ብቻ ሳይሆን ከታች ወደላይ ሃሳቦችን እንዲያፈልቅ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው ሌሎች የጎንዮሽ ውይይቶችም ያስፈልጋሉ፣ ከዚህ በኋላም ወደመግባባት መደረስ አለበት፣ መግባባት ላይ ከተደረሰ የሚቀጥለው ምእራፍ ሀገራዊ እርቅ ነው፣ ከብሄራዊ እርቅ በኋላ ደግሞ ሀገርን የመገንባት ሂደቱን እያጠናከሩ መሄድ የሚል ነው

ይህንንም በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ቁጭ ብሎ የመነጋገርና የመደማመጥ እንዲያም ሲል ደግሞ አንድ መግባባት ላይ መድረስ፤ መግባባት ላይ እንኳን መድረስ ባይቻል መግባባት ባልተደረሰባቸው ጉዳዮች ላይ በመግባባት ኢትዮጵያዊነትን ይዞ ለመቀጠል የተቋቋመ ብሄራዊ የምክክር ኮሚሽን የሕዝቡ በመሆኑ በቀጣይነት ሁሉም ጋር መምጣቱ አይቀሬ መሆኑን ፕሮፌሰር መስፍን ጠቁመዋል

በመሆኑም ይህ ሀገራዊ እሴቶችን የመገንባትና ወደነበሩበት እንዲመለሱ የማድረጉ ጥረት የመንግሥትና የመገናኛ ብዙሃን ሚና ብቻ ሊሆን አይገባም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በተለይ የአሁኑ ትውልድ አባቶቹና እናቶቹ ያቆዩለትን እነዚህን መልካም እሴቶች ወደነበሩበት እንዲመለሱ ከባድ ሃላፊነት አለበት ለዚህም ከአሁኑ ወገቡን ጠበቅ አድርጎ መነሳት አለበት ተብሎ ይጠበቃል ያን ጊዜ የኢትዮጵያ እሴቶች ይፈካሉ

# ትላንትን የሻሩ ወጣቶች

አስናቀ ፀጋዬ

የዘንድሮው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በአስራ አንድ የተለያዩ ዘርፎች በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እየተሰጠ የሚገኝ ሲሆን በመላው አገሪቱ የሚገኙ ከ19 ሚሊዮን በላይ ወጣቶች ተሳትፈዋል። በሚከናወነው በዚሁ የበጎ ፍቃድ አገልግሎትም መንግስትና ህብረተሰቡ ሊያወጡ የሚችሉት 11 ቢሊዮን ብር የሚደርስ ወጪ ይድናል ተብሎ ይጠበቃል። አገልግሎቱም ከሰኔ 15 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 30 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ እንዲከናወን መርሃ ግብር ተይዞለታል።

የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በአረንጓዴ አሻራ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ ሰላም፣ መንገድ ደህንነት፣ ኮቪድ-19 መከላከልና ሌሎችም የጤና አጠባበቅ ስራዎችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስቀረት ግንዛቤ መፍጠር ላይ አተኩሮ እየተሰራበት ነው። ከዚህ ባለፈ የማጠናከሪያ ትምህርት መስጠት፣ የአረጋውያንና አቅመ ደካማ ቤት እድሳት፣ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን መከላከልና ግንዛቤ መፍጠርን ጨምሮ በሌሎች አስራ አንድ ዘርፎች ላይ እየተሰራበትም ይገኛል። በዋናነት ደግሞ የወጣቶችን እርስ በርስ ግንኙነቶች እንዲጠናከሩና አጠቃላይ የወጣቶች ተሳትፎ የጎላ ሚና እንዲኖረው በሰላም ዙሪያ ያተኮሩ ግንኙነቶችም እየተካሄዱ ነው።

በአዲስ አበባ ከተማም ወጣቶች በተለያዩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ውስጥ በመሳተፍ በገንዘብ ሊተመኑ የማይችሉ ከፍተኛ ስራዎችን እያከናወኑ ይገኛሉ። በዘንድሮ በጀት ዓመትም በከተማዋ ነዋሪዎች ዘንድ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ግንዛቤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመምጣቱ በተለያዩ ዘርፎች በተሰራው ሥራ በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ከሶስት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ማዳን ተችሏል።

በእንዲህ አይነቱ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሊወጣ የሚችል ወጪን ማዳን ከቻሉና ለበርካቶች በበጎ ፍቃድ ተደራሽ መሆን ከቻሉት ውስጥ አንዱ በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መርካቶ እህል በረንዳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በሚገኘው ማህበር አንዱ ነው።

ወጣት ሄኖክ ወንድሙ በመርካቶ እህል በረንዳ አካባቢ የጌትነት፣ ሄኖክና ጓደኞቻቸው የደረቅ ቆሻሻ ህብረት ሽርክና ማህበር ሰብሳቢ ነው። በማህበሩ ውስጥ ከስደት፣ ከእስር የተለቀቁና ከተለያዩ ቦታዎች የመጡ 80 የሚጠጉ ወጣቶች እንዳሉ ይናገራል። አብዛኛው ስራዎቻቸውም ከበጎ ፍቃድ አገልግሎት ጋር የተገናኙ መሆናቸውን ይጠቅሳል። የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወደ አገሪቱ ከገባበት ጊዜ አንስቶ በርካታ የበጎ ፍቃድ ስራዎችን እንዳከናወኑም ይጠቁማል።

ከእጅ ማስታጠብ ጀምሮ የማህበሩን አባላት በማሰማራት የተለያዩ ድጋፎች እስከ ማድረግ ድረስ የደረሱ የበጎ ፍቃድ ስራዎችን ማከናወናቸውንም ወጣት ሄኖክ ይገልፃል። ይህ የበጎ ፍቃድ ስራቸው እንደ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ብቻ ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማ ሁለተኛ ደረጃን እንዲቆናጠጡ ያደረገ መሆኑንም ያመለክታል።

በተለይ ደግሞ እህል በረንዳ አካባቢ ከአራቱም አቅጣጫ ተሽከርካሪዎች እህል ጭነው እንደሚመጡና አሽከርካሪዎችና ረዳቶች ስለኮቪድ-19 እምብዛም ግንዛቤ የሌላቸው በመሆኑ ስለበሽታው ግንዛቤ በመስጠት፣ የእጃቸውን ንፅህና እንዲጠብቁ በማስታጠብና የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ እንዲያደርጉ በማድረግ ማህበራቸው ከፍተኛ ስራ እንዳከናወነ ያስታውሳል። በዚህም ከአዲስ አበባ ነጋዴዎች ማህበርና ከአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ምስጋና እንደተቸራቸው ይናገራል።

በሌላ በኩል ደግሞ አቅመ ደካሞችንና አነስተኛ ገቢ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች በበአላትና በሌሎችም ቀናት የመጎብኘትና የመንከባከብ ስራዎችንም የማህበሩ አባላት ሲያከናውኑ እንደነበርም አስታውሶ፤ በክረምትም ወቅት የፈረሱ ቤቶችን አባላትን በመሰብሰብና መልሶ በመጠገንና በማደስ የጉልበት አስተዋፅኦ እንደሚያበረክቱም ወጣት ሄኖክ ይናገራል።

ማህበሩ ከተመሰረተ ሁለት አመት ሊሞላው እንደሆነ የሚናገረው ወጣት ሄኖክ፤ እስካሁን ድረስ የማህበሩ አባላት ከደመወዛቸው በሚያዋጡት ገንዘብ በቋሚነት የሚረዱ ከአስራ አምስት ያላነሱ አቅመ ደካሞችና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እንዳሉ ይገልፃል።

ከዚህ ውጭ በሁለት ዓመታት ውስጥ በአመት ሁለት ጊዜ የአቅመ ደካማና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎችን ቤት እንዳደሱ ይጠቁማል። በዚህም ቢያንስ በአመት ውስጥ ከሰባት ቤት ያላነሰ እድሳት ማድረጋቸውን ይጠቅሳል። የእህል በረንዳና አካባቢውን ፅዳት በመጠበቅ ረገድም ተመሳሳይ ስራ እየሰሩ እንደሚገኙም ይገልፃል። በዚህ የክረምት ወቅትም ከሌላው ጊዜ በተለየ የአካባቢውን ፅዳት ይበልጥ እንደሚጠብቁም ነው ወጣት ሄኖክ የሚናገረው።

በዚህ የክረምት ወቅትም ሶስት የአቅመ ደካማና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ሰዎች ቤት እያደሱ እንደሚገኙም ይናገራል ወጣት ሄኖክ። ነገም ከነገ ወዲያም እንዲህ አይነቱን የበጎ ፍቃድ ስራ ከመንግስት ጋር በመሆን ከመስራት ወደኋላ እንደማይሉም ይገልፃል።

በዚህ ማህበር ውስጥ ያሉት አብዛኛዎቹ ወጣቶች የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ነዋሪና ተወላጆች መሆናቸውን የሚናገረው ወጣት ሄኖክ፤ ከተለያዩ አካባቢዎች መጥተው ማህበሩን በመቀላቀል በዚህ የበጎ ፍቃድ ስራ የሚሳተፉ ወጣቶች እንዳሉም ይጠቅሳል።


ፎቶ፡- በአዩብ ተፈራ
ከግራ ወደቀኝ ወጣት መስፍን አክሊሉ እና ወጣት ሄኖክ ወንድሙ፤

ከዚህ በፊት በዚህ ማህበር ውስጥ ያሉ ወጣቶች በተለያዩ ሱሶች ውስጥ የነበሩ፣ ከስደት የተመለሱና ከእስር የተፈቱ መሆናቸውንና ነገር ግን ማህበሩ ከተመሰረተ በኋላ በአሁኑ ጊዜ የራሳቸውን ቤተሰብ መስርተው ልጆች ወልደው የሚያሳድጉና ቤተሰባቸውንም የሚረዱ ለመሆን እንደቻሉም ያስረዳል። ‹‹ይህም ወጣቶቹ ቀደም ሲል የነበረውን ሕይወታቸውን ከአሁኑ ጋር ሲያወዳደሩት ትልቅ የአእምሮ እረፍት የሚሰጣቸው ነው ይላል›› ወጣት ሄኖክ።

‹‹በዚህ ማህበር ለታቀፉና በፅዳት ስራ ለተሰማሩ አባላት ክፍያ የሚፈፅመው ራሱ ማህበሩ ነው›› የሚለው ወጣት ሄኖክ፤ አባላቱ በሳምንት አንድ ቀን እረፍት ስላላቸው ክፍያው የሚፈፀመው እንደሚመጣው የተሽከርካሪ ብዛት እንደሆነ ይገልፃል። አባላቱ እያንዳንዳቸው በወር እስከ 1ሺ500 ደመወዝ እንደሚከፈላቸውም ይጠቅሳል።

## የአባቶችና እናቶችን ምርቃትና ምስጋና ማግኘት በራሱ ተጨማሪ ደስታ የሚፈጥር እንደሆነም ይናገራል

የአባላቱን ቁጥር በመቀነስ ደመወዙን ከፍ ማድረግ የሚቻል ቢሆንም አብዛኛው ወጣት ስራ አጥ በመሆኑ ሁሉም ስራ እንዲኖረው ለማድረግ ካላቸው ፍላጎት የአባላቱን ቁጥር ማብዛት እንዳስፈለገ ያስረዳል። የአካባቢው ወጣት ሰርቶ እንዲበላና እንዲጠቀም፣ አንዱ አግኝቶ ሌላኛው እንዳያጣ ካላቸው ፍላጎት አንፃር መሆኑንም ይጠቅሳል።

ከነጋዴው ጋር ግንኙነት በመፍጠር ወደ ጎጃም በረንዳ እህል ጭኖ ከሚገባው ተሽከርካሪ በሚሰበስቡት ገንዘብ ራሳቸውን እንደሚደጉሙና ነገር ግን ለአካባቢው ፅዳት ለሳሙናና መጠረጊያ የሚያወጡት ወጪ ከሚያገኙት ገቢ ጋር የሚመጣጠን እንዳልሆነ ይጠቁማል። በየአስራ አምስት ቀኑ የማህበሩ አባላት ደመወዛቸውን እንደሚወስዱም ይጠቅሳል።

በጋራ መመካከርና መስራትን የጀመሩት ማህበሩ ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ መሆኑንም የሚገልፀው ወጣት ሄኖክ አብዛኛው ወጣት በአፍላ እድሜ ክልል ውስጥ ያለ በመሆኑና ስራ ሰርቶ የማያውቅ በመሆኑ ይህን ወጣት ወደ ስራ ለመሳብና ለመምከር ትልቅ ዋጋ እንዳስከፈለ ያስረዳል።

የተወሰነው ወጣት ስራ ላይ ያለ ቢሆንም የተወሰነው ደግሞ በስደት፣ በፀብና በተለያዩ ምክንያቶች በእስር ያሳለፈ በመሆኑ ወደአካባቢው ሲመጣ መግራት እንዳስፈለገ ይገልፃል። ማህበሩ ሲመሰረት ይህን ወጣት በመሰብሰብ መክሮ ወደስራ ለማስገባት ትንሽ ፈተናዎች እንደነበሩትም ያስታውሳል።

ከዛ በኋላ ግን ወጣቶቹ ቀደም ሲል የነበሩበትን ሕይወት እንደአማረሩ ይገልፃል። አብዛኛዎቹም አግብተውና ወልደው ቤተሰቦቻቸውን በገቢ እያስተዳደሩ እንደሚገኙ ይጠቁማል። የተለያዩ ሱሶችን ያቆሙ አባላትን ይዞ ማህበሩ ስራውን እያከናወነ እንደሚገኝም ይጠቅሳል።

ከመደበኛ ስራቸው ባሻገር በተለያዩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች የሚሳተፉ አባሎች ማህበሩ እንዳሉትም ወጣት ሄኖክ ጠቅሶ፤ እስካሁን ድረስ በምድባቸው መሰረት ማታ ላይ አካባቢያቸውን የመጠበቅ፣ መብራት የማስበራት፣ አካባቢውን የመቃኘትና ፀጉረ ልውጥ ሰዎችን የመለየት ስራዎችን እንደሚያከናውኑ ያብራራል። ከዚህ ባለፈ አባላቱ ግንባር ድረስ በመሄድ የመከላከያ ሰራዊቱን አብልተው የመጡበት ጊዜ እንዳለም ይጠቅሳል። በየሶስት ወሩ አባላት ደማቸውን በቋሚነት እንደሚለግሱም ይገልፃል።

‹‹ዋናው ትልቁ እርካት ለሰው ልጅ መድረስ ሲቻል ነው›› የሚለው ወጣት ሄኖክ በጎጃም በረንዳ አካባቢ ገንዘብ ተዋጥቶ ሴቶች በቡና ማፍላት ተሰማርተው ልጆቻቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ሲያስተዳድሩ ማየት ትልቅ እርካታ እንደሚሰማው ይገልፃል። ከዚህ ውጭ የአቅመ ደካሞችና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎችን ቤቶች አድሰው ሲያጠናቅቁና ሰዎቹ ሲደሰቱ ማየት ከእርካታም በላይ ነው ይላል። በዚሁ ስራ የአባቶችና እናቶችን ምርቃትና ምስጋና ማግኘት በራሱ ተጨማሪ ደስታ የሚፈጥር እንደሆነም ይናገራል።

የተለያዩ የመንግስት አካላትም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ወጣቱ በእንዲህ አይነቱ መንገድ ሲሰራና ለመለወጥ ሲታትር ወርዶ ማየትና ማበረታት ብሎም በተለያዩ መንገዶች መደገፍ እንደሚገባ በዚህ አጋጣሚ መልእክቱን ያስተላልፋል።

እንደ ጌትነትና ሄኖክ የወጣቶች ማህበር በአረንጓዴ አሻራ በመሳተፍ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ መሆናቸውንም የሚናገረው ወጣት ሄኖክ የማህበሩ እያንዳንዱ አባላት ቤታቸውን፣ ግቢያቸውንና አካባቢያቸውን እያስዋቡ እንደሚገኙም ይናገራል።

ወጣት መስፍን አክሊሉም ጌትነት፣ ሄኖክና ጓደኞቻቸው የደረቅ ቆሻሻ ህብረት ሽርክና ማህበር አባል ሲሆን ማህበሩ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እጅግ በብዙ የበጎ አድራጎት ስራዎች ላይ ሲሳተፍ መቆየቱንና አሁንም እየተሳተፈ እንደሚገኝ ይናገራል። በተለይ ከኮቪድ-19 ጀምሮ ባለው ሂደት ውስጥ በአካባቢው የእጅ ማስታጠብ፣ ሳኒታይዘር የማቅረብ አልፎም ተርፎ አቅመ ደካማና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎችን የማህበሩ አባላት ከሚያገኙት ገቢ ቀንሰው የምግብ ግብአት ድጋፍ ሲያደርጉ እንደቆዩም ይመሰክራል።

በአሁኑ ጊዜ ደግሞ መንግስት ያዘጋጀውና የአቅመ ደካሞች መኖሪያ ቤቶችን የማደስ መርሃ ግብርን ለማገዝ በዚሁ የክረምት ወቅት ያረጁ ቤቶችን የማደስና መልሶ የመጠገን ስራዎችን ማህበሩ ማከናወኑን ይጠቅሳል። በሌላ በኩል ደግሞ ማህበሩ ከተቋቋመ ጀምሮ በርካታ እርዳታዎችን ለተረጂዎች ሲያደርስ መቆየቱንም ይጠቅሳል። ለአብነትም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው ሲጠይቁ የማህበሩ አባላት ከደመወዛቸው ተቆራጭ በማድረግ ስራ የሚጀምሩባቸው እቃዎች እንዲገዛላቸው የሚደረግ መሆኑንም ያስረዳል።

በዚህም አስራ አምስት የሚሆኑ ሴቶች በተደረገላቸው የገንዘብ ድጋፍ ቡና እያፈሉ፤ ትንሽ ከፍ ብለው ደግሞ ብስኩትና ሻይ እየሸጡ ራሳቸውን እየደጎሙ እንደሚገኙም ወጣት መስፍን ይናገራል። በቅርቡም ለአካል ጉዳተኞች ተሽከርካሪ ወንበሮችን ለመግዛት እንቅስቃሴዎች እንደተጀመሩ ይገልፃል። በቀጣይ ደግሞ ማህበሩ ሊያደርጋቸው የሚያስባቸው በርካታ ነገሮች እንዳሉና ከነዚህ ውስጥም አቅመ ደካማ እናቶችን በመሰብሰብ ቋሚ ድጋፍ ለማድረግ ሀሳብ እንዳላቸውም ይጠቁማል።

‹‹ማህበሩ ቅፅል ስሙ እናት ማህበር ነው የሚባለው›› የሚለው ወጣት መስፍን ይህን ቅፅል ስያሜ ሊያገኝ የቻለው በርካታ መልካም ስራዎችን በመስራቱ እንደሆነ ይናገራል። ሁሉም የማህበሩ አባላት ከነበሩበት አስከፊ ሕይወት ወጥተው በአሁኑ ጊዜ በስራ ላይ በመሆናቸው ተጎዳሁ ብሎ ወደእነሱ የሚመጣን ሰው የሚያይበት መንገድ ስስ መሆኑና በዚህ የተነሳ ወደማህበሩ ለመጣ ሁሉ ድጋፍ ተደርጎለት እንደሚሄድ ያስረዳል።

# የማዕድን ሀብትን በአግባቡ የማልማትና መጠቀም ጥረቶችና ተግዳሮቶቹ - በአማራ ክልል

ስምስም መንግሥቱ

በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ የያዘው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ቢሆንም፣ የማዕድን ዘርፉም ለኢኮኖሚ ዕድገቱ ትልቅ ተስፋ አሳድሯል። ዘርፉ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ከፍ ለማድረግ ከሚኖረው አስተዋጽኦ በተጨማሪ ማዕድኑን ለማውጣት ከሚከናወነው የቁፋሮ ሥራ ጀምሮ በሚፈጥረው የገበያ ሰንሰለት ውስጥ ሰፊ ቁጥር ለበርካታ ሰዎች የሥራ ዕድል በማመቻቸት መንግሥት ለዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሚያደርገውን ጥረት በማገዝ ድርሻው ከፍ ያለ ነው።

በተለይም የቁፋሮ በጋራ መሥራትን የሚጠይቅ በመሆኑ በማህበር በማደራጀት በቀላሉ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ምቹ ዘርፍ ስለመሆኑም ይገልጻል። ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን በማስገኘት በአገር የኢኮኖሚ ዕድገት ሚና ባለው የማዕድን ዘርፍ ላይ ተሰማርተው ከሚሰሩ ማህበራት መካከል በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ደላንታ ወረዳ በ2004 ዓ.ም ማህበር መስርቶ ወደ ስራ የገባው ዋርካዬ የከበሩ ማዕድናት አምራችና ግብይት የህብረት ሥራ ማህበር አንዱ ነው።

በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ደላንታ ወረዳ ውስጥ ፀሐይ መውጫ በሚባል አካባቢ የሚገኘው የዋርካዬ የከበሩ ማዕድናት አምራችና ግብይት የህብረት ሥራ ማህበር መሪ ሊቀ መንበር ደሳለኝ የሞላ እንደሚሉት፤ ማህበሩ በ2004 ዓ.ም በህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ አዋጅ መሠረት ህጋዊ ሆኖ ተቋቁሞ ወደ ሥራ የገባው በአካባቢያቸው የኦፓል ማዕድን ሀብት መገኘቱን ተከትሎ ነው። ይህን የተፈጥሮ ፀጋ በጋራ አልመተው በሚያገኙት ገቢ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻቸውን ለመፍታት፣ አለፍ ብሎም ለአገር ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ ለማበርከት ነው።

ማህበሩ በ25 አባላት ነው የተመሰረተው። አባላቱ የማዕድን ልማት ሥራው በባህላዊ ቁፋሮ የሚከናወን በመሆኑ በወቅቱ ለመነሻ ሥራ የሚሆን ገንዘብ ወይንም ካፒታል ይዘው አልነበረም ወደ ስራው የገቡት፤ እንደ ዶማ፣ አካፋ፣ መዶሻ የመሳሰሉትን ለቁፋሮ ሥራ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች በመያዝ ብቻ ነው ስራውን የጀመሩት። ከልማት ሥራው ዕቅድ አንዱ ተግባር የአባላትን ቁጥር ማብዛት በመሆኑም ማህበሩ ይህን አሟልቷል።

በአሁኑ ጊዜም የአባላቱ ቁጥር ወደ አንድ ሺ ደርሷል። የአባላት ስብስቡም ከ14 አመት በላይ እድሜ ያላቸውን ሁለቱንም ጾታዎች ያካተተ ነው። በማዕድን ቁፋሮ ወቅት በአካባቢው ላይ የሚደርስ ተጽዕኖን ለመቋቋም የአካባቢ ጥበቃ ቢሮውም በማዕድን ማምረት ፍቃድ አሰጣጥ ሂደቱ ላይ ሚናውን ተወጥቷል። በዚህ ሂደት ውስጥ አልፎ ወደ ሥራ የገባው ዋርካዬ የከበሩ ማዕድናት አምራችና ግብይት የህብረት ሥራ ማህበር ከአባላቱ ባለፈ አገርንም የሚጠቅም ተግባር እየተወጣ ይገኛል።

በማዕድን ልማቱ የተገኘውን ጥቅም አቶ ደሳለኝ ከራሳቸው ተሞክሮ በመነሳት ሲገልጹም እሳቸው በትምህርታቸው እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ የመማር ዕድል አግኝተዋል።በተለያየ ምክንያት ከዚያ በላይ መዝለቅ ግን አልቻሉም። ለጥቂት ጊዜያትም ያለ ሥራ ተቀምጠዋል።

የሥራ ዕድል የፈጠረላቸው በአካባቢያቸው የተገኘው የማዕድን ሀብት ነው። ማዕድን ቆፍረው በማውጣት ጥሬ ዕቃውን እሴት ጨምረው ለገበያ ለሚያቀርቡ በመሸጥ የተሻለ ገቢ በማግኘታቸው የተሻለ ኑሮ ለመኖር ከተማ ገቡ፤ በዚያም የመኖሪያ ቤትም ገነቡ። ትዳርም መስርተው ቤተሰብ አፍሩ። የኑሮ መሻሻል ለውጡ የተገኘው ግን ከብዙ ድካም በኋላ ነው።

የማዕድን ቁፋሮ ሥራ ካፒታል የሌለውና ወደ ንግድ ያልገባ በመሆኑ ካመረተ በኋላ ሸጦ በሚያገኘው ገቢ ነው ወደ እድገት ወይንም መለወጥ ደረጃ የሚደርሰው። ለውጡንም የሚያገኘው ባስመዘገበው ልክ ነው።

የማህበሩ አባላት ከልማቱ የሚያገኙት ክፍፍልም በተሳትፎ የሚለካ ነው፤ ጠንክሮ የስራ ጥሩ ገቢ ያገኛል። ጠንክረው በመሥራት ከቁፋሮ ሥራ ወጥተው ጥሬ ዕቃውን በማሻሻል ወይንም እሴት በመጨመር በውጭ ንግድ ላይ የተሰማሩ መሥራች አባላት አሉ። አንዳንዶችም እሴት በመጨመር ሥራ፣ ጥሬ ዕቃውን ከአልሚው በመቀበል እሴት ጨምሮ ለገበያ ለሚያቀርበው በመሸጥ፣ በአዘዋዋሪነት ላይ ይገኛሉ።

> ይህ ሲሆን ከህንድ አገር በውጭ ምንዛሬ በግዥ ወደ አገር የሚገቡትን እንደ ጂብሰም፣ ግራናይት፣ ማርብል ያሉ ለግንባታ ግብአት የሚውሉ የማዕድን ውጤት ምርቶች በአገር ውስጥ መተካት የሚቻልበት ዕድል መኖሩ ተረጋግጧል

በአጠቃላይ ከማህበሩ አባላት ቁጥራቸው ወደ አስር የሚደርስ አባላት ከልማት ዘርፉ ራሳቸውን አሻሽለው ወጥተዋል። 90 በመቶ የሚሆነው የማህበሩ አባል በዘርፉ ኑሮውን ለውጧል። ማሳያዎቹም የኢኮኖሚ አቅም ፈጥሮ ከቤተሰብ ጥገኝነት ወጥቶ በራሱ መተዳደር መቻሉና የሥራ ዘርፉንም በመቀየር ያደረጋቸው ጥረቶች ናቸው።

ይህ በግለሰቦች የተገኘ ጥቅም ነው ያሉት አቶ ደሳለኝ፣ ልማቱ ያስገኘውን አገራዊ ፋይዳ ደግሞ ‹‹በዘርፉ ውስጥ ስለቆየሁ የማዕደን ልማቱ በምን መንገድም ተከናውኖ በአገር ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ አስተዋጽኦ ሊኖረው እንደሚችል አውቃለሁ ሲሉ ይጠቁማሉ። ይሁን እንጂ አቶ ደሳለኝ በዘርፉ ለውጥ በሚያመጣ መልኩ መቶ በመቶ ተሰርቷል የሚል እምነት የላቸውም።

ሥራው አዘዋዋሪና ኤክስፖርተር አለው ቢባልም በልማቱ ተጠቃሚ እየሆኑ ያሉት በህገወጥ የሚንቀሳቀሱ ናቸው በማለትም በዘርፉ የሚስተዋለውን ችግር አቶ ደሳለኝ ይጠቁማሉ። የክልሉ ማዕድንና ቢሮ ይህን የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት እንዳለበትም ነው የሚያስገነዝቡት። የፌዴራል ማዕድን ሚኒስቴር በዘርፉ ዙሪያ የሚሰጠውን መረጃ በተለይም ለውጭ ገበያ የቀረበውን መስማታቸውንና ከደላንታ አካባቢ በኪሎ ግራም የወጣው ኦፓል ማዕድንና ለገበያ የቀረበው መጠን የማይመጣጠን እንደሆነም ይጠቁማሉ። ይህም ህገወጥነቱ ያስከተለው ችግር እንደሆነ ነው ያስረዱት።

ህገወጥነቱ የዋጋ መቀነስ እንደሚያስከትል እንዲሁም ለአገር መግባት ያለበትን የውጭ ምንዛሬ እንደሚያስቀር ገልጸዋል። ከወር በፊት ማዕድን ሚኒስቴር ያለ ይለፍና ደረሰኝ ሳይቆረጥ አልሚው መከፈል ያለበት ክፍያ (የሮያሊቲ ክፍያ) ሳይፈጸም፤ ማዕድኑ ለገበያ እንዲቀርብ የግብይት ሰንሰለትን ለማሳጠር በሚል ያወጣው የአሰራር መመሪያ ደግሞ ይበልጥኑ ዘርፉን ይጎደዋል ይላሉ። አልሚው ከስድስት እስከ ስምንት በመቶ ክፍያ(ሮያሊቲ) ቢቀርለትም እንደ አገር ሲታሰብ ግን ከዘርፉ የሚሰበሰብ ግብርን የሚያሳጣና የሚጎዳ ነው ብለው በመቆርቆር ይጠቁማሉ።

አቶ ደሳለኝ በአካባቢያቸው ስለሚገኘው የማዕድን ሀብት እንዳስረዱት እርሳቸው በልማቱ ላይ በቆዩባቸው ጊዜያቶች የሚያውቁት የማዕድን ሀብት ኦፓል ብቻ ነው። ክልሉም ሆነ የፌዴራል መንግስት በአካባቢው ላይ ጥናትና ምርምር እንዲካሄድ ቢያደርጉ ተጨማሪ ማእድናት ሊገኙ እንደሚችሉ ይገምታሉ። ኦፓል ማዕድንም ቢሆን ክምችቱ ምን ያህል እንደሆነ እንደማያውቁና በመላ በመቆፈር ሲያገኙ መደሰት፣ ሲያጡ ደግሞ ማዘን እንደሆነ ነው የተናገሩት። ምርታማነቱ እንዲያድግና የበለጠ ተጠቃሚ ለመሆን እንዲቻል መንግሥትና ረጅ ድርጅቶች ዘርፉን በተለያየ መንገድ እንዲያግዙ ጠይቀዋል።

የማህበሩ የ2014 በጀት አመት የእቅድ አፈጻጸምና የቀጣይ በጀት አመት እቅድ በተመለከተም አቶ ደሳለኝ እንደገለጹት፤ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በነበረው ጦርነት የአባላት የሥራ መሳሪያዎችና ያፈሩት ሀብት ተዘርፏል። የልማት ሥራውም ተስተጓጉሏል።ማህበሩ መልሶ በመቋቋም ላይ በመሆኑ በ2014 በጀት አመት አፈጻጸም አጥጋቢ የሚባል ውጤት አልተመዘገበም። አሁንም ፀጥታው ሙሉ ለሙሉ የተረጋጋ ባለመሆኑ የወደፊቱንም ውጤታማነት ለማረጋገጥ ወይንም ለመተንበይ ያዳግታል። ባለመረጋጋት ውስጥም ሆኖ መስራቱ በራሱ ውጤት ተደርጎ ይወሰዳል።

የማህበራትን አቅም በመገንባትና አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም በክልሉ የሚገኘውን የማዕድን ሀብት አደራጅቶ ለልማት እንዲውል በማድረግ ረገድ እየተከናወኑ ስላሉ ተግባራት የአማራ ክልል ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ኃይሌ አበበ እንዳስረዱት፤ ከአገራዊ ለውጡ በኋላ በማዕድን ዘርፉ እንደአገር መነቃቃት ተፈጥሯል። ማዕድን የብዝሀ የኢኮኖሚ አማራጮች ተብሎ ከተቀመጡት ዘርፎች መካከል አንዱ ሆኖ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራበት ይገኛል።

ክልሉም ይህንኑ ታሳቢ ባደረገ ከቢሮ የመዋቅር አደረጃጀት ነው ሥራውን የጀመረው ሲሉ አቶ ኃይሌ ይጠቅሳሉ። የቢሮ አደረጃጀቱ የማስፈጸም ብቃትን ለማሳደግ በሚያስችል መልኩ መዋቀሩን፣ በዞንና በወረዳዎችም በተመሳሳይ መዋቅር የተከናወነ መሆኑን ያብራራሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ አደረጃጀቱም ለልማቱ ግብአት የሚሆኑ የስልጠና እገዛዎችንና አስፈላጊ የቁሳቁስ ድጋፎችን ለማጠናከር የሚያስችል ነው። ለአልሚዎች በተለይም በባህላዊ የማዕድን ልማት ላይ ለሚገኙት። የቢሮው ዋና ተግባር ሥራ መፍጠርና ስለሥራው ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። አልሚዎቹ በሚፈልጉት ልክ ባይሆንም ባህርዳር እና ጎንደር ዩኒቨርሲቲዎችን በማስተባበር የቁሳቁስና የክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል።

ቢሮው የጥናት ሥራዎችንም በማከናወን ባከናወነው ተግባርም በአምስት ዘርፎች የተከፈለ ወደ 35 የማዕድን አይነቶች በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች እንደሚገኙ በጥናት ግኝቱ አረጋግጧል። በጥናት የተለዩት የማዕድን አይነቶች ለግንባታ፣ ለኢንዱስትሪ፣ ብረት ነክ፣የኃይል አቅርቦትና የጌጣጌጥ ወይንም የከበሩ ማዕድናት ናቸው።

በነዚህ ዘርፎች በጋራም ሆነ በተናጠል ለማልማት ለሚፈልጉ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በቢሮው ጥረት ማድረጉን አቶ ኃይሌ ይገልጻሉ። እስካሁን ባለው ሂደትም ቢሮው የሲሚንቶ ፋብሪካ ለመገንባት ፍቃድ ለጠየቁ ኩባንያዎች የምርመራ ፍቃድ መስጠቱን ጠቅሰው፣ ከነዚህ መካከል ሁለቱ ኩባንያዎች ሲሚንቶ የማምረት ፍቃድ ወስደው ወደተግባራዊ እንቅስቃሴ መግባታቸውን ነው ያመለከቱት። ኩባንያዎቹ በአንድ አመት ተኩል ጊዜ ውስጥ ወደ ማምረት ሥራ ውስጥ ይገባሉ ተብሎ እንደሚጠበቅም ተናግረዋል።

እንደ ቢሮ ኃላፊው ማብራሪያ፤ ይህ ሲሆን ከህንድ አገር በውጭ ምንዛሬ በግዥ ወደ አገር የሚገቡትን እንደ ጂብሰም፣ ግራናይት፣ ማርብል ያሉ ለግንባታ ግብአት የሚውሉ የማዕድን ውጤት ምርቶች በአገር ውስጥ መተካት የሚቻልበት ዕድል መኖሩ ተረጋግጧል።

ጥሬ ሀብቱ በአማራ ክልል በተለይም በአባይ ሸለቆ ማዕከል ተደርጎ በተለያዩ አካባቢዎች በተከናወነ ጥናት ሁሉም የማዕድን አይነቶች መኖራቸው ተረጋግጧል። በዚህ ዘርፍም ተሰማርተው ወደ ምርት ሥራ የገቡ ኩባንያዎች ምርቶቻቸውን በማቅረብ ከውጭ የሚገባውን ለመተካት ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ቢሮው ከውጭ የሚገቡ የማዕድን ውጤቶችን በአገር ውስጥ መተካት እየሰራ ሲሆን፣ ይሄንንም ከ40 እስከ 50 በመቶ ማሳካት ተችሏል።

እንደ አገር ለግራናይትና ለማርብል ግብአት ግዥ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ይወጣ እንደነበር ያወሱት አቶ ኃይሌ፣ እነዚህን ምርቶች በአገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ፣ በአገር ውስጥ ማምረት መቻሉ ይህን ወጪ ለማስቀረት እንዳገዘና በአገር ውስጥ የመተካት ሥራ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነ ማሳያ መሆኑንም አመልክተዋል።

እንደ አቶ ኃይሌ ማብራሪያ፤ ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች የኃይል ግብአት ሆኖ የሚያገለግለው የድንጋይ ከሰል እንዲሁም የብረትና የተለያዩ የማዕድን ሀብቶች በክልሉ ይገኛል። ኢትዮጵያ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከቱርክና ከደቡብ አፍሪካ በግዥ ወደ አገር ውስጥ የምታስገባውን የድንጋይ ከሰል ምርት በአገር ለመተካት እየተደረገ ባለው እንቅስቃሴም በአማራ ክልል ወሎ አካባቢ ለማምረት እንቅስቃሴ ተጀምሯል።

እነዚህ ተግባራት መንግሥት የማዕድን ዘርፉን አንድ የብዝሀነት የኢኮኖሚ አማራጭ ብሎ በእቅድ የያዘውን ግብ ለማሳካት ያስችላል ይላሉ አቶ ኃይሌ። እቅዱን ለማሳካት በሚከናወኑት ተግባራት እንቅስቃሴዎች አልጋ በአልጋ እንደማይሆኑና ተግዳሮት እንደማያጣውም ጠቁመዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ አንዱ ተግዳሮት ማዕድናቱ በሚገኙባቸው አካባቢዎች የመሠረተ ልማት አቅርቦት አለመኖር ነው። ለልማት ሥራው ፋብሪካ ለሚያቋቁሙ ኩባንያዎች የኃይል አቅርቦት መጓተት ሌላው ተግዳሮት ነው። ልማቱ ለአካባቢውና ለአገር ጠቃሚ እንደሆነ ተገንዝቦ አስፈላጊውን ትብብር አለማድረግም በማህበረሰቡ በኩል የሚስተዋል የግንዛቤ ችግር ነው። ህገ ወጥነትም ሌላው ችግር ሲሆን፣ በተለይም በኦፓል ማዕድናት ላይ የኮንትሮባንድ ችግር ይስተዋላል። ችግሮቹን በመለየትና መፍትሄ ለመስጠት በቢሮ በኩል ጥረት ቢደረግም ተከታታይ ሥራ እንደሚያስፈልግ አቶ ኃይሌ ገልጸዋል።

በተለይም ህገወጥነት (ኮንትሮባንድ) አልሚዎችም በስፋት ያነሱት ጉዳይ በመሆኑ ቢሮው ለመከላከል ያስቀመጠው አቅጣጫ ምን እንደሆነ አቶ ኃይሌ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ እንዳብራሩት፤ በቀበሌ ደረጃ የማዕድን ግብረ ኃይል በመቋቋሙ ግብረ ኃይሉ ውጤታማ ሥራ እንዲሰራ ማድረግ ይጠበቃል። ሌላው የኦፓል ማዕድን መሸጫ ማዕከል በመገንባት ግብይቱን ህጋዊ ማድረግ፣ ክትትልና ቁጥጥሩን ማጠናከር ነው። የጌጣጌጥ ማዕድናት ግብይትን በተመለከተ ከብሄራዊ ባንክ ጋር በመነጋገር በየአካባቢው ከሚገኙ ባንኮች ጋር በማስተሳሰር ግብይቱ እንዲከናወን ማድረግ ሌላው መፍትሄ ነው።

የፌዴራል ማዕድን ሚኒስቴር የማዕድን ሀብቶች ማስተዋወቂያ የማዕድን ጋለሪ እንዳዘጋጀው ሁሉ እንዲህ ያለውን ተሞክሮ በክልላቸው በመተግበር ረገድ እቅድ ይኖራቸው እንደሆንና በ2014 በጀት አመት ከማዕድን ዘርፉ የተገኘ ገቢን በተመለከተ አቶ ኃይሌ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲያብራሩም፣ የማዕድን ሙዚየም ለመገንባት፣ የማዕድን ፍኖተ ካርታ ለማዘጋጀት፣ የማዕድን ልማት ቀጠናዎች ለማዘጋጀትና ወደ 20ሺ ካሬ ኪሎ ሜትር በካርታ (ማፕ) ላይ ማሳየት በእቅድ ከተያዙ ተግባራት መካከል መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በ2014 በጀት አመት ከክልሉ 13ሺ140 ኪሎ ግራም የተዋበና ያልተዋበ ኦፓል ለውጭ ገበያ መቅረቡን ጠቅሰዋል፤ ከጌጣጌጥ ማዕድናት አምስት ነጥብ ሰባት ሚሊየን ዶላር ገቢ በማስገኘት በአገር ኢኮኖሚ ላይ አስተዋጽኦ ማበርከት መቻሉን አስታውቀዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## እፎይ

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

ለምን እንደሆነ አላውቅም አራት ሰአት አለፍ ሲል ይደብተኛል ድብርቴን የምሸሸው የሆረር ፊልም በማየትና በደረቴ በመተኛት ነው የዛሬውም አራት ሰአት እንደተለመደው ምርግ ነበር አብሮኝ ከሚኖረው ፍታወቅ ጋር አዋተን በገዛናት ፍራሽ ላይ በደረቴ ተኝቼ የረፋድ ድብርቴን አጎንብሼ አሳልፋለው በጣቴ መሬት እየጫርኩ የማላውቀውን ነገር ማዲያው ላይ እጽፋለው በዚህ መሀል ስሜን ከውጪ ሲጠራ ሰማሁት.. ሮቤል? አንተ ሮቤል?

ነፍሴ ሳቀች.. ጀምበር ፈንጥቃ ስፍራዋን ለረፋድ ስትለቅ ማንም የማያስቀኝ ሰው ነበርኩ ከሰአት እስኪሆን ማለዳ በጉያው ውስጥ የሸሸገው የአራት ሰአት አጋንት ከላዬ ላይ ጮሆ እስኪወጣ ድረስ ማንም የማያዝናናኝ ሰው ነበርኩ ለዘመናት የተላመድኩት ድባቴዬ የት እንደገባ ሳላውቀው በሄመን ድምጽ ነቃሁ ‹ሮቤል.. አንተ ሮቤል? ድምጽዋ ወዳለሁበት እየቀረበ መጣ ከአልጋዬ ላይ እንዴት እንደተፈናጠርኩ አላውቅም ራሴን በሩ ላይ አገኘሁት እኔ ስወጣ እሷ ስትገባ ተጋጨን መቼም የማይደገም ግጭት አይኖቼን የት ላድርጋቸው? አፈርኳት ፊት ለፊቴ በግንባሬ የተገጨ ግንባሯን እያሻሸች ቆማለች አይኖቿ የእፍረት ዝናር ታጥቀው ያዩኛል ጡቶቿ በስስ የቤት ውስጥ ፒጃማ ተወድረው ደረቴ ላይ ተነጣጥረዋል ከንፈሯ ሩብ ያህሉ በጥርሶቿ በቁንጥ ተነክሶ ተደቅኖብኛል አይኖቼን የት ላድርጋቸው?

መደናበሬን አይታ ይሆን እንጃ ‹ቤት ማንም የለም ናና ተጫወት› ብላኝ ወደ ቤት ተመለሰች

ከበሩ ላይ አልተንቀሳቀስኩም ፊልም የሚመስለውን አጋጣሚ በአእምሮዬ እየመለስኩ ቆሜአለው ቆይቼ ሳስበው ከመጋጨትም በላይ የሆነ ነገር ያስተናገድን ይመስለኛል ደረቴ ላይ አሁንም ድረስ የሚሰማኝ ደስ የሚል የውጋት ህመም አለ.. በጡቶቿ የተወጋሁት ጉንጬ ላይ ጳጉሯ የገረፈኝ አንዳች የሚያክል ሰንበር አለ ራሴን በመስተዋት ሳየው ቀይ የከንፈር ቀለም ከንፈሬ ላይ ተለጉዶ ነበር ይሄ እንዴት ሆነ? ደስ የሚል የሚያሳፍር ሳቅ ሳኩኝ ሰው እንዴት በአንድ ጊዜ ደስ የሚልና የሚያሳፍር ሳቅ ይስቃል? ሄመንን አፈርኳት መንገድ ላይ ስንገናኝ ለመሳሳም የተቀጣጠርን እንጂ ለመጋጨት የተገናኘን አንመስልም ነበር

አንዳንድ ቀኖች አሉ.. የሰው ልጅ አስቦና ተዘጋጅቶ የማይደግማቸው አንዳንድ አጋጣሚዎች አሉ እንዴት እንደመጡ፣ እንዴት እንደሆኑ ታስቦ የማይደረስባቸው ከሄመን ጋር የተጋጨንበትን የዛሬውን ቀን ጻፍኩት መቼም እንዳይረሳኝ ስለምፈልግ

እፎይ ብያለው.. መቼም እንደዛሬ እፎይ ብዬ አላውቅም አንዳንድ ድምጾች አሉ ከሕይወት እስራት፣ ከመኖር ስብራት ነጻ የሚያወጡ አንዳንድ አንደበቶች አሉ ከካህን አፍ ጥመው ለጆሮ የሚጣፍጡ አንዳንድ ቀኖች አሉ ሚሊዮን ዘመነ ፍዳን ሽረው አርነት የሚያወጡ እንዲህ ባለው የድባቴ ጊዜ ውስጥ ድንገት ተከስተው ወደ ገነት የሚወስዱኝ አንዳንድ ድምጮች አሉ.. የሄመንን አይነት ድምጽ ነፍሴ ሳቀች በሕይወት ውስጥ ነፍስ የምትስቅበት ቅጽበት አለ እላለሁ .. ለእኔ ያ ቅጽበት የሄመን ጥሪ ነው ለእኔ ያ ቅጽበት ቆንጆ ሴት በርህን ቆርቁራ ካለህበት ስትመጣ ነው ዓለም ከነግሳንግሷ ከፊቴ ላይ ገለል ያለችልኝ ሄመን ስትጠራኝ ነው

ተነስቼ ወደነ ሄመን ቤት ሄድኩ ሁሌ እንዲህ እንደአሁኑ ቤት ብቻዋን ስትሆን ትጠራኛለች እንደ እኔ አራት ሰአት ይደብራት ይሆን አላውቅም ብዙ ቀን ደብቶኝ በተኛሁበት የአራት ሰአት ማግስት ላይ ጠርታኝ ቤት ሄጄ አውቃለሁ እነሄመን ቤት ከተከራየሁ ስምንተኛ ወሬን ይዣለሁ በወር አንድ ጊዜ የሚመጣ ፍታወቅ የሚባል ጓደኛ ቢኖረኝም አብሮኝ እንዳለ አልቆጥረውም እሷም ይሄን ብቸኝነቴን ስለምታውቅ ነው መሰለኝ ቤተሰቦቿ ወጣ ሲሉ መጥህ ተጫወት ብቻዬን ነኝ ትለኛለች

ቤት ስገባ ለስለስ ያለ ሙዚቃ ተቀበለኝ.. ዛሬም ሚኪያ እየዘፈነች ነው ሁሌ እዛ ቤት ጠርታኝ ስሄድ በሚኪያ በላይነህ ሙዚቃ ነው የምትቀበለኝ እዛ ቤት የሚኪያ በላይነህ ሙብዛት አልገባህ እንዳለኝ ወደ ሳሎን አቀናሁ ሄመን ከሙዚቃው ጋር አብራ እየሞዘቀች ቅድም በተላተምኩበት ፒጃማዋ አገኘኋት

‹ምነው ብቻሽን.. እነማዘር የት ሄደው ነው? አልኳት ድምጼን አጥፍቼ ከምገባ ብዬ

‹ማዘር ክፍለ ሀገር ሄዳለች...

‹እና ብቻሽን ነሻ!..

‹አዎ ሰሞኑን ብቻዬን ነኝ...› አለችኝ በሚያሳዝን ድምጽ  ድምጽዋ ውስጥ ከብቸኝነት የገዘፈ ሌላ ብቸኝነትን አደመጥኩ እኔ ሆኜ እንጂ ፍታወቅ ቢሆን ከዚህ ንግግሯ ውስጥ ብዙ እውነቶችን መዞ ያወጣ ነበር ብዙ ጊዜ ነገር አይገባህም ይለኛል እሱ ብቻ አይደለም እስከዛሬ የተዋወኳቸው ሴቶች ነገር አይገባህም ሲሉኝ አድምጫለው የሄመን ‹ሰሞኑን ብቻዬን ነኝ› ማለቷ ከወሬ ባለፈ ምን ማለት እንደሆነ ሳይገባኝ ዝም አልኩ ወር ሙሉ ከአጠገቤ ሲርቅ ያልናፈቀኝ ጓደኛዬ በአይኔ ላይ አንጃበበ

‹አባዬም እንደምታውቀው በስራ ምክንያት አምሽቶ ነው የሚገባው..› ሳልጠይቃት ነገረችኝ ይሄን ብላ ትታኝ ወደሚቀጥለው ክፍል አመራች ምሳ እየሰራች እንደሆነ ከሚሰነፍጠኝ የወጥ ሽታ ተረዳሁ ማዕድ ቤቱ ከሳሎኑ ፊት ለፊት ስለሆነ እንቅስቃሴዋ ሁሉ ይታየኛል እኔ ሳሎን ሶፋ ላይ ሆኜ እሷ ማዕድ ቤት ሆና እስኪበቃኝ ቀላወጥኳት

ቤት ጠርታኝ የሆነ የምወደውን ነገር ሳታደርግልኝ ቀርታ አታውቅም ሁሌም አዲስ ነገሬ ናት ማዕድ ቤት በስስ ፒጃማዋ ውስጥ የማይታየኝ ነገር የለም እንደ ጣዝማ ማር የጠየመ ገላዋ የጠለለ የምንጭ ውሃ ይመስል ነበር ቀይ ፓንት፣ ጥቁር ጡት ማሲያዣ ደረቷንና ወገቧን ዞረው ሳይ ሀጢአት ተሰማኝ እዛ ቤት ስገባ የማያቸው የሁልጊዜም ትዕይንቶቼ ነበሩ ብዙ ጊዜ አትገባኝም.. የማልረዳት ሴት ናት ለምንና እንዴት እንደምታስበኝ ሳላውቅ በምትሆነው መሆን እጨነቃለሁ ቆይ አንድ ሴት ለአንድ ወንድ እህት ብቻ መሆን አትችልም? እኛ ወንዶች ሴት ልጅ ለፍቅር ብቻ ነው የቀረበችን ብለን እንድናስብ የሚያደርግ የተሳሳተ ሶፍት ዌር የጫነብን ማነው?


በእጇ ምሳ ይዛ ወደሳሎን ተመለሰች የዛሬ አዲስ ነገር አብሬአት ምሳ ሙብላት ነው ከእሷ ጋር ምሳ ሙብላት ምን እንደሚመስል ዛሬ ላየው ነው እስከዛሬ ቤታቸው ሄጄ በቻዬን ነበር ስበላ የነበርኩት ከእሷ ጋር ሙብላትን በእለተ ሀሙስ ከጌታ ጋር በአንድ መዐድ ከመቀመጥ ጋር አገናኘሁት ሳላውቀው ሄመንን እንደ እህት አምኖ መቀበል እየከበደኝ መጣ አውቃም ይሁን ሳታውቅ የምታደርገው ነገር ወደማላውቅ ደስታ እየወሰደኝ ነው

እጄን አስታጥባኝ የመጀመሪያውን ጉርሻ ወደ እኔ ስትሰነዝር የሆንኩትን አረሳውም ጉርሻዋ ብርቅ ሆኖብኝ ለረጅም ጊዜ አላመጥኩት ያን ጉርሻ ወደ ሆዴ ሳልሰድ ቀን ሙሉ እያላመጥኩት ብውል በወደድኩ ነበር ከዛ በኋላ ያልቆጠርኳቸውን ብዙ ጉርሻዎች አጎረሰችኝ ሳላጎርሳት ዝም ብዬ ሙብላት ጀመርኩ ባልተቀየመ ልብ ማጉረሷን ተያያዘችው

እፎይ አልኩ..

ሕይወት እፎይ ማያ ሲኖራት ምን እንደምትመስል ያን ቀን አወኩ ፍቅር የሕይወት ሱስ ነው.. ሳላውቀው በምታደርግልኝ ነገር ሄመንን ወደድኳት ነፍሷ እፎይ ማያዬ ሆኖ አረፈ...

# ዓለም አቀፍ




## የኬንያ ምርጫ ውጤት አሸናፊ በጉጉት እየተጠበቀ ነው

ባለፈው ማክሰኞ ለብሔራዊ ምርጫ ድምጻቸውን የሰጡት ኬንያውን ውጤቱን በጉጉት እየተጠባበቁ ነው። የድምጽ ቆጠራው አሁንም እየተካሄደ ባለበት በአሁኑ ወቅት ለፕሬዚዳንትንት የቀረቡት ዋነኞዎቹ ዕጩዎች በጠባብ የድምጽ ልዩነት እየተፎካከሩ ነው።

በአፍሪካ ጠንካራ ምጣኔ ሀብት፣ የፍትሕ እና የምርጫ ሥርዓት እንዲሁም የመገናኛ ብዙኃን ካላቸው ጥቂት አገራት መካከል አንዷ በሆነችው ኬንያ የሚካሄደው ምርጫ ውጤት ከአገሪቱ ባሻገር በአህጉሪቱ ውስጥ ከፍተኛ ትኩረትን የሚያገኝ ነው።

22 ሚሊዮን የሚደርስ ሕዝብ በመራጭነት የተመዘገበበትና 14 ሚሊዮኑ ድምጹን በሰጠበት በዚህ ምርጫ ኬንያውያን ለፕሬዚዳንት፣ ለግዛቶች አስተዳዳሪዎች፣ የብሔራዊ እና የአካባቢያዊ ምክር ቤቶች አባላትን ለመምረጥ ድምጽ ሰጥተዋል። ከዚህ መካከል ከፍተኛ ትኩረትን የሳበው ግን አገሪቱን ለቀጣይ አምስት ዓመታት በፕሬዚዳንትነት ለመምራት የሚደረገው ፉክክር ነው።

ይህ ፉክክር በዋናነት በአሁኑ ወቅት የአገሪቱ ምክትል ፕሬዚዳንት በሆኑት ዊሊያም ሩቶ እና በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መካከል የሚደረገው ፉክክር ከባድ እንደሚሆን ቀድሞም ተጠብቆ ነበር። በሁለቱ ግዙፍ ፖለቲከኞች መካከል ያለው ፉክክር ግጭትን እንዳያስከትል የብዙዎች ስጋት ሲሆን፣ እስካሁን በነበረው ሁኔታ ግን ይህ ነው የሚባል የጎላ የፀጥታ ችግር በተፎካካሪዎቹ ደጋፊዎች መካከል አልተከሰተም።

ነገር ግን ድምጽ ተሰጥቶ ቆጠራው ከተጀመረ ሁለተኛው ቀን ቢሆንም እስካሁን ሩቶ እና ራይላ ከመራጮች ባገኙት ድምጽ ግልጽ የበላይነት ማግኘት አልቻሉም። በምርጫው ድምጽ ከሰጡት መራጮች መካከል ወደ ግማሽ የሚሆነው ድምጽ የተቆጠረ ቢሆንም ልዩነታቸው ጠባብ የሚባል በመሆኑ ኬንያውያን ውጤቱን በጉጉት እየጠበቁ ነው።

በርካታ ሚሊዮኖች ለቀጣዩ አምስት ዓመታት አገራቸውን የሚመራውን ፕሬዚዳንት መርጠው ውጤቱን እየተጠባበቁ ይገኛሉ። የኬንያ የምርጫ ኮሚሽን ሊቀ መንበርም ምርጫ ከተደረገበት ማክሰኞ ነሐሴ 03 እስከ ቀጣዮቹ ሰባት ቀናት ድረስም የምርጫውን ውጤት ማሳወቅ እንደሚኖርባቸው የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

## ዶናልድ ትራምፕ በተከፈተባቸው ምርመራ ዙሪያ ቃሳቸውን ለመስጠት አሻፈረኝ አሉ

የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ በኒውዮርክ በቤተሰብ ንግድ ዙሪያ መንግሥት እያደረገ ለሚገኘው ምርመራ ቃላቸውን እንዲሰጡ ቢጠየቁም ፍቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። ትራምፕ ትናንት በኒውዮርክ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ጽህፈት ቤት ከተከፈተባቸው ምርመራ ጋር በተያያዘ ቃል ለመስጠት የተገኙ ቢሆንም ጠቅላይ አቃቤ ሕግን በመኮነን ምላሽ ሳይሰጡ ቀርተዋል።



የትራምፕ የንግድ ድርጅት ብድር እና የግብር እፎይታን ለማግኘት የተሳሳተ የሀብት መጠን አሳውቋል የሚል ክስ በመንግሥት ቀርቦበታል። ሆኖም ትራምፕ ይህንን ክስ አይቀበሉትም። ትራምፕ ቃለ መሃላ ፈጽመው የእምነት ክህደት ቃላቸው የሚሰጡበት ስፍራ ላይ የተገኙ ሲሆን በንባብ ባሰሙት መግለጫ የኒውዮርክ ጠቅላይ አቃቤ ሕጓን ተችተዋል።

እዚህ ለመድረስ ብዙ ዓመታት እና ሚሊዮን ዶላሮች ወጥቷል ያሉ ሲሆን "በአሜሪካ ሕገ መንግሥት በተጠቀሰው መብት መሰረት ቃሌን ላለመስጠት ወስኛለሁ" ብለዋል። ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ትናንት ረቡዕ በተካሄደው ቃል የመስጠት ሂደት ላይ ትራምፕ ቃላቸውን እንዲሰጡ ተጠይቀው ነበር ብሏል። ሆኖም የቀድሞው ፕሬዚዳንት ቃላቸውን ሳይሰጡ መቅረታቸውን አረጋግጧል።

"የትኛውም የአመራር ደረጃ ጠቅላይ አቃቤ ሕጓ ሕግ እና እውነታን መሰረት አድርገው ይቀጥላሉ" ያለው መግለጫው ምርመራው እንደሚቀጥል ገልጿል። ይህ የትራምፕ ድርጊት የተሰማው በፍሎሪዳ የሚገኘው ቤታቸው ኤፍ ቢ አይ ፍተሻ ካደረገ ከቀናት በኋላ ነው።

የኒውዮርክ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ምርመራ እያደረገ በሚገኝበት የፍትሃብሔር ወንጀል ሲሆን በማንታን አውራጃ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ጽህፈት ቤት ደግሞ በወንጀል ሊያስጠይቅ የሚችል ክስ ተመስርቶባቸዋል። የሕግ አዋቂዎች ትራምፕ ቃላቸውን ከመስጠት አሻፈረኝ ያሉበት ምክንያት ምን አልባት ምላሻቸው በምርመራ ወቅት የራሳቸው ቃል ለምርመራው አጋዥ እንዳይሆን ሰግተው ነው የሚል ግምታቸውን ሰጥተዋል።

የቀድሞ ፕሬዚዳንት ራሳቸውን እንዲከላከሉ ጥሪ የቀረበላቸው ሰዎች ክስ በሚመሰረትባቸው ጊዜ ራሳቸውን እንዲከላከሉ በሚያዘው የሕግ አግባብ መሰረት ሲሆን ተከሳሾች ቃላቸውን ያለመስጠት መብታቸው ግን የተጠበቀ ነው። የቃል መስጠቱ ሂደቱ ረጅም እረፍትን ጨምሮ አራት ሰዓት እንደፈጀ ጠበቃቸው ተናግረዋል።

እየተቀረጸ በነበረው የቃል መስጠት ሂደቱ ላይ ትራምፕ ቃል ያለመስጠት መብታቸውን በተመለከተ በንባብ አሰምተዋል። በተጨማሪም በንባባቸው ጠቅላይ አቃቤ ሕጓን ኮንነዋል። ለሚጠየቁት ሁሉም ጥያቄዎች ተመሳሳይ ምላሽ ሲሰጡም እንደነበር ቢቢሲ ዘግቧል።

# ስፖርት





## የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሴቶች ቡድን በሴካፋ ለመሳተፍ ወደ ታንዛኒያ አቀና

**ቦጋለ አበበ**

የ2014 የኢትዮጵያ ሴቶች ፕሪሚየር ሊግ አሸናፊ የሆነው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሴቶች እግር ኳስ ክለብ ታንዛኒያ በሚካሄደው የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ክለቦች ቻምፒዮና ላይ ለመሳተፍ ትናንት ወደ ታንዛኒያ አቅንቷል።

በኢትዮጵያ ሴቶች እግር ኳስ ውድድር ታሪክ የፕሪሚየር ሊጉን ዋንጫ በርካታ ጊዜ በማንሳት ስኬታማ የሆነው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቡድን ታንዛኒያ በሚካሄደው የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ክለቦች ቻምፒዮና ላይ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ መዘጋጀቱ ታውቋል። "ጀግኖች አትሌቶቻችን የአገራቸውን ስም በዓለም አቀፍ መድረክ ከፍ እንዳደረጉት ሁሉ እኛም እንደ አትሌቶቹ የአገራችንን ስም በመልካም ለማስጠራት ተዘጋጅተናል" ሲሉም የቡድኑ አባላት ወደ ታንዛኒያ ከማቅናታቸው በፊት ገልፀዋል።

ቡድኑ ከቀናት በፊት በተዘጋጀለት የሽኝት ሥነ ሥርአት ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዝዳንት አቤ ሳኖ፣ የእግር ኳስ ክለቡ በውድድሩ ላይ የተሳካ ጊዜ እንዲያሳልፍ በመመኘት ለስኬት እንዲበቃም አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል። በሥነ ሥርአቱ ላይ የክለቡ አሠልጣኝ እና አምበል ከባንኩ ፕሬዝዳንት የባንዲራ ርክክብ በማድረግ በድል ለመመለስ ቃል ገብተዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሴቶች እግር ኳስ ክለብ በምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ክለቦች ቻምፒዮና ላይ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ይረዳው ዘንድ ስድስት ተጫዋቾችን ከአገር ውስጥ ክለቦች ማስፈረሙ የሚታወስ ነው። ክለቡ ከነሐሴ 7 እስከ 22 ቀን 2014 ዓ.ም በሚካሄድው ቻምፒዮና ላይ ውጤታማ ለመሆን አራያት አዶንግ፣ ኒቦኚ የን፣ ቅድስት ዘለቀ፣ መሳይ ተመስገን፣ ብርቄ አማረ እና ናርዶስ ጌትነትን ማስፈረሙ ይታወቃል።



የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሴቶች ቡድን በአገር ውስጥ ያለውን ስኬት በሴካፋ ለመድገም ተዘጋጅቷል፣

ዘንድሮ ለ2ኛ ጊዜ በሚካሄደው በምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ክለቦች ቻምፒዮና ላይ ስምንት ክለቦች ተሳታፊ ይሆናሉ። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አንደኛው ተሳታፊ ክለብ ሲሆን የዩጋንዳው ሺ ኮርፖሬትቷ የታንዛኒያው ሲምባ ኲዊንስ፣ የደቡብ ሱዳኑ ዬ ጀይንት ስታርስ፣ የዛንዚባሩ ዋሪየር ኲዊንስ፣ የቡሩንዲው ፎፊላ ፒ ኤፍ፣ የሩዋንዳው ኤኤስ ኪጋሊ፣ የጅቡቲው ጂአር ኤፍሲ በውድድሩ እንደሚሳተፉ ታውቋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በውድድሩ በምድብ አንድ ከዛንዚባሩ ዋሪየርስ እንዲሁም ከብሩንዲው ፎፊላ እና ከሩዋንዳው ኤኤስ ኪጋሊ ጋር ተደልድሏል። የመጀመሪያ ጨዋታቸውንም ከዛንዚባሩ ክለብ ዋሪየርስ ጋር ያደርጋሉ። ንግድ ባንኮች ቀሪ የምድብ ማጣሪያ ጨዋታቸውን ደግሞ ከብሩንዲው ፎፊላ እና ከሩዋንዳው ኤኤስ ኪጋሊ ጋር በተከታታይ የሚያደርጉ ይሆናል። በ2022 ወርሃ ጥቅምት ሞሮኮ ለምታስተናግደው የአፍሪካ የሴቶች ቻምፒየንስ ሊግ ውድድር ለማለፍ በሚደረገው የምስራቅ አፍሪካ ክለቦች ማጣሪያም ንግድ ባንኮች ውድድራቸውን በበላይነት ካጠናቀቁ በአፍሪካ የሴቶች የክለቦች ውድድር የሚሳተፉ ይሆናሉ።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሴቶች እግር ኳስ ቡድን ኬኒያ ላይ ተዘጋጅቶ በነበረው የመጀመሪያው የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ክለቦች ቻምፒዮና ላይ የ2ኛ ደረጃን ይዞ ማጠናቀቁ ይታወሳል።

## የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ቅድመ ዝግጅት እየተጠናቀቀ ነው

16ኛውን የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ(ሲቲ ካፕ) በደመቀ መልኩ ለማካሄድ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች እየተጠናቀቁ መሆናቸው ተገለፀ።

የአዲስ አበባ ከተማ እግር ኳስ ፌዴሬሽን በየአመቱ የሚያዘጋጀውና ዘንድሮ ለ16ኛው ጊዜ የሚካሄደው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ውድድርን በአማረና በደመቀ መልኩ ለማካሄድ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን እያጠናቀቀ መሆኑን ገልጿል።

ፌዴሬሽኑ ትላንት በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል በውድድሩ ተካፋይ ከሚሆኑ አምስት ክለቦች ጋር ውይይት ያደረገ ሲሆን ውድድሩ ደረጃውን የጠበቀና ክለቦች ወቅታዊ አቆማቸውን የሚፈትሹበት ጠንካራ ውድድር ለማድረግ ስምምነት ላይ ደርሰዋል።

በተመልካች ዘንድ በየአመቱ በጉጉት የሚጠበቀው እና አዳዲስ ነገሮች ጨምሮ የሚመጣው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ዘንድሮ የውጭ ክለቦችን የሚያሳትፍ ሲሆን በየውድድሩ የሚሰጠውን የሽልማት መጠኑንንም ፌዴሬሽኑ እንደሚያሳድግ በውይይቱ ላይ ተጠቁሟል።

የውይይት መድረኩን የመሩት የፌዴሬሽኑ ፕሬዘዳንት አቶ ደረጀ አረጋ፣ የፌዴሬሽኑን ጥሪ አክብረው በ16ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ላይ ለመሳተፍ ፍቃደኛ የሆኑትን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ስፖርት ክለብ፣ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ስፖርት ክለብ፣ መከላከያ ስፖርት ክለብ፣ ለገጣፎ ለገዳዲ ስፖርት ክለብን እና አዳማ ስፖርት ክለብን አመስግነው በቀጣይ በኢትዮጵያ ቤት ኪንግ ፕሪሚየር ሊግ ከሚሳተፉ ጠንካራ ክለቦችም በዚህ ውድድር ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ፌዴሬሽኑ እየተነጋገረ መሆኑን አሳውቀዋል።

16ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ውድድር ጳጉሜን 4/2014 ዓ.ም ለመጀመር በውይይቱ ላይ መግባባት የተቻለ ሲሆን ትክክለኛ ጊዜውን ቀኑ ሲቃረብ ፌዴሬሽኑ በጋዜጣዊ መግለጫ እንደሚያሳውቅ ጠቁሟል።

16ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫን ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ለማካሄድ የአዲስ አበባ ከተማ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ከጎፈሬ ትጥቅ አምራች ድርጅት ጋር ስምምነት መፈፀሙ ይታወቃል።


## የጨረታ ማስታወቂያ

የሚዛን አማን ከተማ አስተዳደር ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ለሴ/መ/ቤቶች አገ/ት የሚውል ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ፈርኒቸር ዕቃዎች፣ ሞተር ሳይክል፣ደንብ ልብስ፣ የጽ/መሳሪያ እና የጽዳት ዕቃዎች ግዥ በጨረታ አወዳድሮ ግዥ መፈፀም ይፈልጋል::

በጨረታው መወዳደር የምትፈልጉ ተጫራቾች የሚከተሉትን መስፈርቶች በማሟላት መወዳደር ይችላሉ::

1. ተጫራቾች በተሰማሩበት የሥራ መስክ የዘመኑን ግብር የከፈሉና የታደሰ ንግድ ፈቃድ እና የሥራ ፍቃድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል::
2. የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ መሆን አለባቸው::
3. ተጫራቾች የአቅራቢነት ምዝገባ ሰርተፍኬት ማቅረብ ይኖርባቸዋል::
4. ተጫራቾች የዕቃዎቹን ሙሉ ዝርዝር የያዘ የጨረታ ሰነድ በግዥ ኬዝ ቲም የሥራ ሂደት ቢሮ በመቅረብ የማይመለስ ለእያንዳንዱ ሰነድ ብር 100/አንድ መቶ ብር/ በመግዛት መወዳደር ይችላሉ::
5. ተጫራቾች የጨረታ ዋጋቸውን ሞልተው በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ለዚሁ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ሁለት ኮፒ እና አንድ ኦርጅናል በአንድ ፖስታ በማድረግ ለዚሁ በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል::
6. ጨረታው የሚከፈተው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ21 ተከታታይ ቀናት በኋላ ባለው የሥራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው ቀን ከጠዋቱ 3:30 ላይ ታሽጎ በዚያው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል::
7. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ 10,000/አስር ሺ ብር/ በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ/ በጥሬ ገንዘብ ማስያዝ ይጠበቅባቸዋል::

ማሳሰቢያ፡- መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::

**ለበለጠ መረጃ ስልክ ቁጥር 047 3360124**

**የሚዛን አማን ከተማ አስተዳደር ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት**

## ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

የአጋሮ ከተማ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ከዚህ በታች የተዘረሩትን እቃዎች በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም በጨረታው ላይ ለመሳተፍ የምትፈልጉ ተጫራቾች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በማሟላት መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የእቃዎቹ አይነትና የጨረታ ማስከበሪያ (ሲፒኦ) መጠን**

ሎት 1- የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ማስያዝ ያለባቸው የጨረታ ማስከበሪያ(ሲፒኦ) ብር 20,000
ሎት 2-የተለያዩ የጽህፈት እቃዎች ማስያዝ ያለባቸው የጨረታ ማስከበሪያ(ሲፒኦ) ብር 15,000
ሎት 3-የተለያዩ የግንባታ እቃዎች ማስያዝ ያለባቸው የጨረታ ማስከበሪያ(ሲፒኦ) ብር 20,000
ሎት 4-የተለያዩ ሞተር ሳይክሎች ማስያዝ ያለባቸው የጨረታ ማስከበሪያ(ሲፒኦ) ብር 15,000
ሎት 5-የተለያዩ የተሽከርካሪ ጎማዎች ማስያዝ ያለባቸው የጨረታ ማስከበሪያ(ሲፒኦ) ብር 20,000

**የመወዳደሪያ መስፈርቶች**

1) በጨረታው ላይ መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች በዘርፉ የንግድ ስራ ፍቃድ ያላቸውና የ2014 ዓ.ም የስራ ዘመን ፍቃዳቸውን ያደሱ (አዲስ ያላቸው) መሆን አለባቸው
2) ተጫራቾች ቫት ተመዝጋቢ መሆን አለባቸው፡፡ ቫት ተመዝጋቢ ስለመሆናቸው የቫት ሰርተፊኬት ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
3) የአቅራቢነት ሰርተፊኬት ማቅረብ አለባቸው::
4) ማህበር ከሆኑ ስለ-ህጋዊ ሰውነታቸው የሚገልጽ ሰርተፊኬት የ2014 የታደሰ (አዲስ) ከአነስተኛና ጥቃቅን ቢሮ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡:
5) ተጫራቾች ከዚህ በላይ በተመለከተው መሰረት የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋጠ ሲፒኦ (ማህበር ከሆኑ እንደ ሲፒኦ የሚያገለግል ደብዳቤ በተወዳደሩበት የጨረታ አይነት ለተወዳደሩበት መስሪያ ቤት ማለትም ለአጋሮ ከተማ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ካደራጃቸው አካል በግልጽ የተጻፈ ኦርጅናል ደብዳቤ) ማስያዝ አለባቸው፡፡
6) ተጫራቾች ተጫርተው የሚያሸንፉትን ዕቃ ወይም እቃዎች በራሳቸው የትራንስፖርት ወጪ እስከ አጋሮ ከተማ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ድረስ ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡
7) ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ የማይመለስ ብር 300 (ሶስት መቶ ብር) በመክፈል ከአጋሮ ከተማ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 7 መውሰድ ይችላሉ፡፡
8) ጨረታው ከወጣበት ቀን 6/12/2014 ጀምሮ 15 የሥራ ቀናት እስከ 26/12/2014 ቆይቶ በዚሁ ቀን 4:30 ሰዓት ላይ ተዘግቶ ተወዳዳሪዎች ወይም ተወካዮች ባሉበት ቢሮ ቁጥር 7 ከቀኑ 5፡00 ሰዓት ላይ የሚከፈት ይሆናል፡፡
9) መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ መሰረዝ ይችላል፡፡

**ለበለጠ መረጃ፡- 047 221 3021/047 221 1061/047 221 2261**

**መደወል ይችላሉ።**

**የአጋሮ ከተማ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት**